ኤሌክትሮኒክ ደረሰኝ ሥርዓት አስተዳደር መመሪያ
ቁጥር 1142/2018

Electronic Invoicing System Administration Directive
Directive No. 1142/2026

አዲስ አበባ፤

ሐምሌ፤ 2018 ዓ.ም

መመሪያ ቁጥር 1142/2018

የኤሌክትሮኒክ ደረሰኝ ሥርዓት አስተዳደር መመሪያ

የታክስ አስተዳደሩን ዘመናዊ፣ የአገልግሎት አሰጣጡን ቀልጣፋና ውጤታማ ለማድረግ እንዲሁም የታክስ ስወራን ለመከላከል እየተተገበረ ያለውን ስራ ከሚዘረጋው የቴክኖሎጂ ስርዓት አንፃር የተጣጣመ እንዲሆን በማስፈለጉ፤

ታክስ ከፋዩ የኤሌክትሮኒክ ደረሰኝ ስለሚጠቀምበት ሁኔታ፣ የኤሌክትሮኒክ ደረሰኝ ሥርዓት ስለሚፈቀድበት ሁኔታ እና በአጠቃቀም ላይ ሊደረግ ስለሚገባው ጥንቃቄ በዝርዝር መግለጽ በማስፈለጉ፤

የአስፈጻሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 1263/2014 አንቀጽ 27 ላይ ለሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ የተሰጠውን ስልጣንና ተግባራት በተሟላ ሁኔታ ለመተግበር አስፈላጊ በመሆኑ፣

የራሳቸውን የሽያጭ መመዝገቢያ ሥርዓት አልምተው ወይም ከአልሚዎች ገዝተው በማስፈቀድ ለሚጠቀሙ ታክስ ከፋዮች፣ የኤሌክትሮኒክ የሽያጭ መመዝገቢያ ስርዓት እውቅና በማግኘት ለመሸጥ እና የኤሌክትሮኒክ የሽያጭ መመዝገቢያ ሥርዓት አገልግሎት አቅራቢ ሆነው አገልግሎት ለሚያቀርቡ ድርጅቶች የክትትልና ቁጥጥር ሥርዓት መዘርጋትና አሰራራቸውን በህግ መወሰን ተገቢ በመሆኑ፤

Directive No. 1142/2026

Electronic Invoicing System Administration Directive

WHEREAS, it has become necessary to ensure that the ongoing efforts to modernize tax administration, enhance service delivery efficiency and effectiveness, and prevent tax evasion are harmonized with the technological systems being deployed;

Whereas, it has become necessary to specify the conditions in detail under which taxpayers shall utilize electronic invoices, the requirements for the authorization of the Electronic Invoice Registration System, and the precautions to be taken during its implementation;

WHEREAS, it is necessary to fully implement the powers and duties assigned to the Ministry under Article 27 of the Definition of Powers and Duties of the Executive Organs Proclamation No. 1263/2021;

Whereas, it has become necessary to establish a monitoring and control system and legally define the procedures for taxpayers who develop their own sales registration systems or purchase and obtain authorization for use, for entities seeking recognition to sell Electronic Sales Registration Systems, and for organizations providing services as electronic Electronic Sales Registration system service providers;

የገቢዎች ሚኒስቴር የአስፈጻሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 1263/2014 አንቀጽ 19(4) እና በፌደራል ታክስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 983/2008 አንቀጽ 19(4) በተሰጠው ስልጣን መሰረት ይህንን መመሪያ አውጥቷል።

Accordingly, the Ministry of Revenues has issued this directive pursuant to the authority granted under Article 19(4) of the Definition of Powers and Duties of the Executive Organs Proclamation No. 1263/2021 and Articles 19(4) of the Federal Tax Administration Proclamation No. 983/2016.

ክፍል አንድ

ጠቅላላ ድንጋጌዎች

SECTION ONE

General Provisions

1. **አጭር ርዕስ**

ይህ መመሪያ **"የኤሌክትሮኒክ ደረሰኝ አስተዳደር ስርዓት መመሪያ ቁጥር 1142/2018"** ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

1. **Short Title**

This Directive may be cited as the **"Electronic Invoicing System Administration Directive No.1142/2026"**

2. **ትርጓሜ**

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር ለዚህ መመሪያ አፈፃፀም፤

1/ "ኤሌክትሮኒክ ደረሰኝ" ማለት በሚኒስቴሩ እውቅና የተሰጠውን የሽያጭ መመዝገቢያ ሶፍትዌር በመጠቀም ለሚከናወን ግብይት የሚሰጥ ዲጂታል የግብይት ሰነድ ነው።

2/ "የኤሌክትሮኒክ ደረሰኝ መመዝገቢያ ሥርዓት" ማለት በሚኒስቴሩ ተዘጋጅቶ የቀረበ ሶፍትዌር ሆኖ ደረሰኝን በማዕከል ለመመዝገብ፣ ለማረጋገጥና መረጃ ለማጠናቀር፣ ከታክስ ከፋዮች ስርዓት ጋር መረጃ ለመቀበል፣ ባለስልጣኑ እና ለታክስ ከፋዮች ከደረሰኝ ጋር ተያያዥ የሆኑ ልዩ ልዩ አገልግሎቶችን ለማቅረብ የሚያስችል ነው።

3/ "የተመዘገበ ኤሌክትሮኒክ ደረሰኝ" ማለት በኤሌክትሮኒክ ደረሰኝ መመዝገቢያ ሥርዓት

2 **Definitions**

In this Directive, unless the context requires otherwise:

1/ "Electronic Invoice" means a digital transaction document issued for a transaction carried out using a sales registration software authorized by the Ministry;

2/ "Electronic Invoice Registration System" means a software developed and deployed by the Ministry to centrally register, verify, and process invoice data; to receive information through integration with taxpayers' systems; and to provide various invoice-related services to the Authority and taxpayers;

3/ "Registered Electronic Invoice" means an invoice that has been registered in the Electronic Invoice Registration System and assigned

ተመዝግቦ የደረሰኝ ምዝገባ ቁጥር እና ፈጣን መላሽ ኮድ የተሰጠው ደረሰኝ ነው።

an Invoice Registration Number (IRN) and a Quick Response Code (QR Code);

4/ "የሽያጭ መመዝገቢያ "ሶፍትዌር" ማለት ራሱን ችሎ ለሽያጭ መመዝገቢያ ብቻ የሚያገለግል የሽያጭ ነቁጣ ወይም ከሌሎች የንግድ አሳላጭ ስርዓቶች እንደ የድርጅት ሀብት እቅድና አስተዳደር እንዲሁም መሰል ሥርዓቶች ጋር የተጣመረ ወይም በልዩ ልዩ መሳሪያዎች ላይ የተጫነ ሆኖ ታክስ ከፋዩ ሽያጩን ለመመዝገብ የሚጠቀምበት እና የሽያጭ መረጃዎችን በቀጥታ በኤሌክትሮኒክ ደረሰኝ ስርዓት ለማስተላለፍ እና ለመመዝገብ የሚያስችል እንዲሁም ደረሰኝ ለማተም ወይም ለገዢው በዲጂታል አማራጭ ማድረስ የሚያስችል ሶፍትዌር ነው።

4/ "Sales Registration Software" means a standalone Point of Sale (POS) system used solely for registering sales, or a system integrated with other business processing systems such as Enterprise Resource Planning (ERP) and similar platforms, or installed on various devices, used by a taxpayer to register sales; and which is capable of directly registering and transmitting sales data to the Electronic Invoice System, as well as printing invoices or delivering them to the buyer through digital alternatives;

5/ "የሽያጭ መመዝገቢያ ሥርዓት አገልግሎት (Software as a Service)" ማለት ታክስ ከፋዮች ለአገልግሎት ተመዝግበው፣ የአገልግሎት ክፍያ በመክፈል (subscription) አገልግሎት የሚያገኙበት የሽያጭ መመዝገቢያ ሥርዓት ነው ።

5/ "Sales Register System Service (Software as a Service)" means a sales register system through which taxpayers obtain service on a subscription basis

6/ "የሽያጭ መመዝገቢያ ስርዓት አቅራቢ" ማለት ማለት እውቅና የተሰጠውን የሽያጭ መመዝገቢያ ሥርዓት በሽያጭ ለታክስ ከፋይ የሚያቀርብ አቅራቢ ነው።

6/ "Sales Registration System Supplier" means a supplier that provides an accredited sales register system to a taxpayer through sale.

7/ "የሽያጭ መመዝገቢያ ሥርዓት አገልግሎት አቅራቢ" ማለት እውቅና የተሰጠውን የሽያጭ መመዝገቢያ ሥርዓት አገልግሎት ታክስ ከፋዩን የአገልግሎት ክፍያ በማስከፈል (subscription) የሚያቀርብ አቅራቢ ነው።

7/ "Sales Register System Service Provider" means a provider that provides an accredited sales register system service to a taxpayer on a subscription basis.

8/ "በኢኮሜርስ ወይም በዲጂታል ገበያ ቦታ(platform) የሚሰጥ የኤሌክትሮኒክ ደረሰኝ" ማለት ሻጭና ገዥን ወይም አገልግሎት ፈላጊንና አቅራቢን ለማገናኘት በሚያገለግል የዲጂታል መድረክ ላይ ለተፈፀመ ግብይት የሚሰጥ ደረሰኝ ነው።

8/ "Electronic receipt issued on an e-commerce or digital marketplace (platform)" means a receipt issued for a transaction on a digital platform that serves to connect a seller and a buyer, or a service seeker and a provider.

9/ ኢኮሜርስ ወይም ዲጂታል ገበያ ቦታ አንቀሳቃሽ" ማለት ኢኮሜርስ ወይም ዲጂታል ገበያ ቦታን ለተጠቃሚዎች የሚያቀርብ አገልግሎት አቅራቢ ነው።

10/ "አቅራቢ" ማለት የሽያጭ መመዝገቢያ ስርዓት አቅራቢ ወይም የሽያጭ መመዝገቢያ ሥርዓት አገልግሎት አቅራቢ ወይም ኢኮሜርስ ወይም ዲጂታል ገበያ ቦታ አገልግሎት ሰጪዎች ማለት ነው።

11/ "ታክስ ከፋዩ ለራሱ ብቻ የሚጠቀምበት ሶፍትዌር" ማለት ታክስ ከፋዩ ከገበያ ገዝቶም ይሁን አልምቶ ለራሱ ሥራ ብቻ የሚጠቀምበት እና እውቅና ያለው አቅራቢ የሌለው ሆኖ በሚኒስቴሩ ፈቃድ የተሰጠው የሽያጭ መመዝገቢያ ሶፍትዌር ነው።

12/ "የክላውድ የሽያጭ መመዝገቢያ ሥርዓት" ማለት ታክስ ከፋዮች ግብይታቸውን ለመመዝገብ የሚያስችል በባለስልጣኑ ተዘጋጅቶ የቀረበ የሽያጭ መመዝገቢያ ስርዓት ነው።

13/ "ከቀጥታ ግንኙነት ውጭ ሥራ ማስቀጠያ ስርዓት" ማለት በልዩ ልዩና በሚታወቁ ምክንያቶች የታክስ ከፋይ ሲስተም ከኤሌክትሮኒክስ ደረሰኝ መመዝገቢያ ስርዓት ጋር ያለው የቀጥታና ወዲያውኑ ግንኙነት በሚቋረጥበት ወቅት ግብይትን ለውስን ጊዜ ለማስቀጠል የሚያስችል አማራጭ መንገድ ነው።

14/ "የዱቤ ሽያጭ ደረሰኝ" ማለት ዕቃ ወይም አገልግሎት በዱቤ ለሚገዙ ሰዎች ሻጭ የሚሰጠው የግብይት ማረጋገጫ ሰነድ ሆኖ የተጨማሪ እሴት ታክስ ደረሰኝ፣ የኤክሳይዝ ታክስ ደረሰኝ እና ከእነዚህ ታክሶች ነፃ ለሆኑ ግብይቶች የሚሰጥ የዱቤ ሽያጭ ደረሰኝን ያካትታል፣

9/ "e-Commerce or Digital Market Place Operator" means a service provider that provides an e-Commerce or Digital Market Place to users;

10/ "Supplier" means a Sales Registration System Supplier, or a Sales Registration System Service Provider,or an e-Commerce or Digital Market Place Service Provider;

11/ "Software for Exclusive Use by a Taxpayer" means a sales registration software authorized by the Ministry, which a taxpayer either develops or purchases from the market for their own exclusive business operations, and for which there is no recognized third-party supplier;

12/ "Cloud Sales Registration System" means a sales registration system developed and provided by the Authority that enables taxpayers to register their transactions;

13/ "Offline Business Continuity System" means an alternative method that enables the continuation of transactions for a limited period when the direct and real-time connection between the taxpayer's system and the Electronic Receipt Registration System is interrupted due to various recognized reasons;

14/ "Credit Sales Invoice" means a transaction confirmation document issued by a seller to persons purchasing goods or services on credit, and includes Value Added Tax (VAT) receipts, Excise Tax receipts, and credit sales receipts issued for

transactions exempt from these taxes;

15/ "የእጅ በእጅ ሽያጭ ደረሰኝ" ማለት ዕቃ ወይም አገልግሎት ለሚገዙ ሰዎች ሻጭ የሚሰጠው የግብይት ማረጋገጫ ሰነድ ሆኖ የተጨማሪ እሴት ታክስ ደረሰኝ፣ የኤክሳይዝ ታክስ ደረሰኝ እና ከነዚህ ታክሶች ነጻ ለሆኑ ግብይቶች የሚሰጥ ሰነድ ነው።

15/ "Cash Sales Invoice" means a transaction confirmation document issued by a seller to persons purchasing goods or services, and includes Value Added Tax (VAT) receipts, Excise Tax receipts, and documents issued for transactions exempt from these taxes;

16/ "የገንዘብ መቀበያ ደረሰኝ" ማለት በታክስ ከፋዩ ስም በጥሬ ገንዘብ፣ በቼክ ወይም በባንክ ለተከፈሉ ወይም ገቢ ለተደረጉ ለንግድ ስራው ብድር፣ ቅድመ ክፍያ፣ የዱቤ ክፍያ እና ሌሎች ገቢዎች ወይም ገዥ ቀደም ሲል በዱቤ የተሸጠለትን ዕቃ ወይም የአገልግሎት ክፍያ ሲፈፀም የሚሰጥ ማረጋገጫ ሲሆን ዕቃ ወይም አገልግሎት ሽያጭ ስለመፈጸሙ የሚሰጥ ደረሰኝን አይጨምርም።

16/ "Cash Receipt" means a confirmation issued for payments made in cash, check, or bank transfer in the name of a taxpayer for business loans, advance payments, credit settlements, and other incomes, or when a buyer settles a payment for goods or services previously sold on credit; however, it does not include a receipt issued for the actual sale of goods or services;

17/ "ከተከፋይ ሂሳብ ላይ ለተቀነሰ ግብር የሚሰጥ ደረሰኝ" ማለት ዕቃ ወይም አገልግሎት ግዢ የፈፀመ ሰው ከክፍያው ላይ ግብር ለተቀነሰበት ሰው የሚሰጥ የክፍያ ማረጋገጫ ሰነድ ነው።

17/ "Withholding Tax Receipt" means a payment confirmation document issued by a person who has purchased goods or services to the person from whose payment the tax has been deducted;

18/ "የግዢ ማረጋገጫ ደረሰኝ" ማለት በታክስ ባለስልጣኑ ዕውቅና ለተሰጣቸውና ደረሰኝ ሊቀርብላቸው ላልቻሉ ግብይቶች ግዢ ስለመፈፀሙ ለማረጋገጥ በገዢው ተዘጋጅቶ በወጪ ማስረጃነት የሚቀርብ ሰነድ ነው።

18/ "Purchase voucher" means a document prepared by a buyer and submitted as evidence of expense to confirm the purchase of goods or services for transactions authorized by the Tax Authority where a standard receipt cannot be provided;

19/ "በገዢው ተይዞ ለሚከፈል የተጨማሪ እሴት ታክስ የሚሰጥ ደረሰኝ" ማለት

19/ "Receipt for Value Added Tax Withheld by the Buyer" means a

ታክሱን ቀንሰው ስለማስቀረታቸው የሚሰጥ የማረጋገጫ ሰነድ ነው፡፡

confirmation document issued to verify that the tax has been withheld and retained by the buyer;

20/ "የታክስ ዴቢት ወይም የታክስ ክሬዲት ሰነድ" ማለት የተጨማሪ እሴት ታክስ የሚከፈልበት ግብይት ዋጋ በአዋጅ ቁጥር 1341/2016 አንቀጽ 43 እና 44 መሰረት ማስተካከያ ሲያስፈልገው ለታክሱ በተመዘገበ አቅራቢ ለገዢ የሚሰጥ የክሬዲት ወይም የዴቢት ማረጋገጫ ሰነድ ነው፡፡

20/ "Tax Debit or Tax Credit Note" means a credit or debit confirmation document issued by a registered supplier to a buyer, where the value of a transaction subject to Value Added Tax requires an adjustment in accordance with Articles 43 and 44 of Proclamation No. 1341/2024;

21/ "ባለሥልጣን" ማለት የገቢዎች ሚኒስቴር ሲሆን፣ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር፣ የድሬዳዋ አስተዳደር እና የክልሎችን ገቢ ሰብሳቢ መስሪያ ቤቶችን ይጨምራል፡፡

21/ "Authority" means the Ministry of Revenues, and includes the Revenues Bureaus of the Addis Ababa City Administration, Dire Dawa City Administration and regional states;

22/ "ሚኒስቴር ወይም ሚኒስትር" ማለት የገቢዎች ሚኒስቴር ወይም ሚኒስተር ማለት ነው፡፡

22/ "Ministry or minister " means the Ministry or minister of Revenues ;

23/ "በቋሚነት የሚሰራ ድርጅት" ማለት በፌዴራል የገቢ ግብር አዋጅ የተሰጠውን ትርጉም ይይዛል፡፡

23/ "Permanent Establishment" means the definition given under the federal income tax proclamation.

24/ በዚህ መመሪያ ውስጥ ትርጉም ያልተሰጣቸው ቃላት በታክስ ህግ የተሰጣቸውን ትርጉም ይይዛሉ፡፡

24/ Terms not defined in this Directive shall have the meanings given to them under the Tax Law

25/ በዚህ መመሪያ በወንድ ጾታ የተገለፀው ለሴትም ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

25/ In this Directive, provisions expressed in the masculine gender shall also apply to the feminine gender.

3. የተፈፃሚነት ወሰን

1/ ይህ መመሪያ በታክስ ህግ መሰረት ደረሰኝ በሚሰጡ ታክስ ከፋዮች፣ የሽያጭ መመዝገቢያ ስርዓት አቅራቢዎች፣ የሽያጭ መመዝገቢያ ሶፍትዌሩን ለራሳቸው ብቻ በሚጠቀሙ ታክስ ከፋዮች፣ የሽያጭ መመዝገቢያ ስርዓት አገልግሎት አቅራቢዎች፣የኢኮሜርስ እና ዲጂታል የገበያ ቦታ አንቀሳቃሾች ላይ፤

2/ የተጨማሪ እሴት ታክስ አዋጅ ቁጥር 1341/2016 በአንቀፅ 3 መሰረት ተፈፃሚ በሚሆንበት ታክስ በሚከፈልበት ግብይት ላይ ፤

ተፈፃሚ ይሆናል።

3. Scope of Application

1/ This Directive shall apply to taxpayers that issue invoice as per the tax law, Sales Registration System Suppliers, a Taxpayer that use Sales Registration System Exclusively, Service Providers (Software as a Service), and e-Commerce and Digital Marketplace Operators.

2/ It shall be applicable to taxable transactions where Value Added Tax is applicable in accordance with Article 3 of Proclamation No. 1341/2024.

ክፍል ሁለት

የሽያጭ መመዝገቢያ ሥርዓት ፈቃድ አሰጣጥ፣ እድሳት፣ ግዴታዎች እና ስረዛ

SECTION TWO

Licensing, Renewal, Obligations, and Cancellation of Sales Registration Systems

4. አጠቃላይ የሽያጭ መመዝገቢያ ሥርዓት ፈቃድ አሰጣጥ ሁኔታ

1/ የሽያጭ መመዝገቢያ ሥርዓት ፈቃድ የሚሰጠው በባለስልጣኑ የኤሌክትሮኒክ ደረሰኝ መመዝገቢያ ሥርዓት ጋር በመገናኘትና የተስማሚነት መስፈርት በማሟላት የግብይት መረጃ ማስተላለፍና መቀበል መቻሉ በሚከተሉት መስፈርቶች መሰረት በፍተሻ መረጋገጥ አለበት።

4. General Conditions for Licensing of Sales Registration Systems

1 The licensing of a Sales Registration System shall be subject to verification through inspection, ensuring its capability to transmit and receive transaction data by integrating with the Authority's Electronic Invoice Registration System and fulfilling conformity

requirements based on the following criteria:

ሀ) በሽያጭ መመዝገቢያ ሶፍትዌር የሚያዘጋጀው ደረሰኝ ቢያንስ በተጨማሪ እሴት ታክስ ደንብ ቁጥር 570/2017 አንቀፅ 20 የተዘረዘረውን የደረሰኝ ይዘት የያዘ እና ከዚህ መመሪያ ጋር በተያያዘው የደረሰኝ ናሙና ላይ የተመለከቱትን ዝርዝር መረጃዎች የሚይዝ ሆኖ ሲገኝ፤

a) Where the invoice prepared by the Sales Registration Software contains, at a minimum, the receipt contents listed under Article 20 of the Value Added Tax Regulation No. 570/2024, and includes the detailed information specified in the sample invoice (receipt) attached to this Directive;

ለ) የሽያጭ መረጃን ግብይቱ እንደተከናወነ ወዲያውኑ ለባለሥልጣኑ በትክክል መረጃ መላክ ሲችል እና ምላሹንም ለተጠቃሚው በትክክል ማሳየት ሲችል፣

b) Where the system is capable of transmitting accurate transaction data to the Authority in realtime as the transaction occurs, and correctly displaying the response to the user;

ሐ) ለኤሌክትሮኒክ ደረሰኝ መመዝገቢያ ሥርዓቱ መረጃ ልኮ እና ትክክለኛነቱ ተረጋግጦ የኢንቮይስ እና የደረሰኝ መለያ ቁጥሮች እና ፈጣን መላሽ መለያ ሲያገኝ ብቻ ኢንቮይስ እና ደረሰኝ የሚሰጥ መሆኑ ሲረጋገጥ፣

c) Where it is verified that the system issues an invoice or receipt only upon transmitting data to the Electronic Receipt Registration System, confirming its validity, and obtaining an Invoice Reference Number (IRN), a Receipt Reference Number (RRN), and a Quick Response (QR) Code;

መ) የኤሌክትሮኒክ ደረሰኝ መመዝገቢያ ሥርዓቱ የሚሰጠውን የኢንቮይስ እና የደረሰኝ መለያ ቁጥሮች እና ፈጣን መላሽ መለያ በትክክል እና ተነባቢ አድርጎ ማተም ወይም ማሳየት ሲችል፣

d) Where the system is capable of printing or displaying the Invoice Reference Number (IRN), the Receipt Reference Number (RRN), and the Quick Response (QR) Code issued by the Electronic Receipt Registration System accurately and in a legible format;

ሠ) የግብይቱን ተገቢ የሆኑ ታክስ አይነቶች መለየትና በትክክል ማስላት መቻሉ ሲረጋገጥ፣

e) Where it is verified that the system is capable of identifying the appropriate tax types for the transaction and calculating them accurately;

ረ) እንደ ደረሰኙ ዓይነት የሚደረግን የመመዝገብ ጥያቄ በትክክል መላክ ሲችል እና መልሱንም ለተጠቃሚው ማሳየት ሲችል፣

ሰ) የደረሰኝ ስረዛ በሚያስፈልግበት ወቅት የስረዛ ጥያቄን በትክክል መላክ ሲችል እና መልሱንም ለተጠቃሚው ማሳየት ሲችል፣

ሸ) የሽያጭ መመዝገቢያ ስርዓቱ ለለያቸው ተጠቃሚ ታክስ ከፋዮች የሚጠቀሙባቸውን የደረሰኝ አይነቶችና የግብር ስሌት በትክክል ተግባራዊ ለማድረግ ማስቻሉ ሲረጋገጥ፤

ቀ) የተመዘገበን ደረሰኝ በዲጂታል አማራጮች (በኢሜይል፣ አጭር የስልክ መልዕክት ወይም ሌላ) ለገዥ መላክ እና እንደ ገዥው ፍላጎት አትሞ መስጠት ሲችል፤

2/ የሽያጭ መመዝገቢያ ሥርዓቱ በመረጃ ልውውጥ፣ ማከማቸት እና ደህንነት በተመለከተ የሚከተሉትን ማሟላት ይኖርበታል፤

ሀ) ከኤሌክትሮኒክ ደረሰኝ መመዝገቢያ ሥርዓቱ ጋር ለመገናኘት፣ መረጃ ለማለዋወጥ እና መረጃ ለመመስጠር የሚጠቀምበትን ልዩ ልዩ መረጃዎችና የሚስጥር ቁልፎች ፈቃድ ያለው ተጠቃሚ ብቻ የሚያስተካክልበት እና የሚያሻሽልበት አገልግሎት ሲኖረው እንዲሁም ሌሎች ተጠቃሚዎች ማየትም ሆነ መቀየር እንደማይችሉ ሲረጋገጥ፣

ለ) ከኤሌክትሮኒክ ደረሰኝ መመዝገቢያ ሥርዓቱ ጋር የሚደረገውን የመረጃ

f) Where the system is capable of accurately transmitting registration requests based on the specific type of receipt and correctly displaying the response to the user;

g) Where the system is capable of accurately transmitting a cancellation request when a receipt needs to be cancelled and correctly displaying the response to the user;

h) Where it is verified that the Sales Registration System accurately implements the respective types of invoices and correctly calculates the applicable tax types for its targeted taxpayers;

i) Where the system is capable of sending a registered receipt to the buyer through digital options (email, SMS, or others) and providing a printed copy upon the buyer’s request;

2 The Sales Registration System shall fulfill the following requirements regarding data exchange, storage, and security:

a) Where it is verified that the system provides a feature enabling only authorized users to configure or update various connection data and encryption keys used for communicating and exchanging data with the Electronic Invoice Registration System, while ensuring that other users are strictly prohibited from viewing or modifying such information;

b) Where it is verified that the system is capable of recording

ልውውጥና የተጠቃሚዎችን የየዕለት ድርጊቶች፣ ድርጊቱ የተፈጸመበትን ጊዜ እና ድርጊቱን የፈጸመውን ግለሰብ የሚያሳይ ክዋኔ ኦዲት ሪፖርት መመዝገብና ለተፈቀደለት አካል ማሳየት የሚችል መሆኑ ሲረጋገጥ፣

an operation audit log that tracks data exchanges with the Electronic Invoice Registration System, daily user activities, the timestamps of such actions, and the identity of the individual who performed them, and ensuring such logs are accessible to authorized entities;

ሐ) የታክስ ባለስልጣኑ በፈለገ ጊዜ መረጃውን ለማውጣት፣ ለማየት እና ኦዲት ለማድረግ የሚያስችል መሆኑ ሲረጋገጥ፣

c) Where it is verified that the system enables the Tax Authority to extract, view, and audit data at any time as required;

መ) በቂ መረጃ የማከማቸት አቅም እና የታክስ መረጃ በህግ ለተደነገገው ጊዜ ያክል ማስቀመጥ የሚያስችል መሆኑ ሲረጋገጥ።

d) Where it is verified that the system has sufficient storage capacity and the capability to retain tax information for the duration prescribed by law;

3/ የሽያጭ መመዝገቢያ ሥርዓት አጠቃቀምና ለስራ ለማዘጋጀት የሚከተሉትን ማሟላት ይኖርበታል

3 The Sales Registration System shall fulfill the following requirements regarding its utilization and operational readiness:

ሀ) የተጠቃሚውን ታክስ ከፋይ ስም፣ የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር፣ አድራሻ እና ሌሎች መለያዎችን ሶፍትዌሩ ለሥራ ዝግጁ በሚሆንበት ወቅት ብቻ ለመሙላት የሚያስችል ሲሆን፣

a) Where the system allows the entry of the taxpayer's name, Taxpayer Identification Number (TIN), address, and other identifiers only during the operational readiness (On-Boarding) stage;

ለ) የሽያጭ መመዝገቢያ ስርዓቱ ተጠቃሚዎች እንደተሰጣቸው ሚናና ተግባር የተመጠነ አገልግሎት አሰጣጥ ስርዓት ሲኖረው፣

b) Where the Sales Registration System features a Role-Based Access Control (RBAC) mechanism that provides services tailored to the specific roles and functions assigned to each user;

ሐ) ተጠቃሚዎች በአሰራር ወይም ሌላ ምክንያት ችግር ሲያጋጥማቸው ለተጠቃሚዎቹ አግባብ ያለው ችግሩን የሚገልፅ መልዕክት ማሳየት የሚችል መሆኑ ሲረጋገጥ፤

c) Where it is verified that the system is capable of displaying appropriate error messages to users when operational or other technical difficulties occur;

መ) የሽያጭ መመዝገቢያ ስርዓቱ ተጠቃሚዎች ብቻ በመለያ ስም እና የሚስጥር ቁልፍ ወይም ሌላ የመጠቀሚያ ፈቃድ በመጠቀም አገልግሎቱን ለማግኘት የሚፈቅድ መሆኑ ሲረጋገጥ፣

4/ ከቀጥታ ግንኙነት ውጭ የሚሰራ የሽያጭ መመዝገቢያ ስርዓት ሲሆን የሚከተሉትን መስፈርቶች ማሟላት ይኖርበታል፤

ሀ) በባለስልጣኑ የተዘጋጀውን ከቀጥታ ግንኙነት ውጭ ሥራ ማስቀጠያ ስርዓት መተግበሩ በፍተሻ ሲረጋገጥ፣

ለ) ሥርዓቱ በተለያዩ ምክንያቶች ተቋርጦ የነበረው የቀጥታና ወዲያውኑ ግንኙነቱ እንደቀጠለ ከቀጥታ ግንኙነት ውጭ የተፈጸሙ ግብይቶችን መረጃ ማስተላለፍና ማስመዝገብ መቻሉ ሲረጋገጥ፣

ሐ) ከላይ በፊደል ተራ "ሀ" እና "ለ" የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ይህንን ከቀጥታ ግንኙነት ውጭ ግዴታ የሚሆንባቸው ዘርፎች ከዚህ መመሪያ ጋር በአባሪነት ተያይዘዋል።

5/ የሽያጭ መመዝገቢያ ስርዓቱ በተንቀሳቃሽ የሽያጭ መመዝገቢያ ነቁጣ፣ ወይም የእጅ ስልክ፣ ወይም ሌሎች ዘመናዊ ተንቀሳቃሽ መሳሪያዎች ላይ ተጭኖ የሚሰራ ሲሆን፦

ሀ) መሳሪያው ያለበትን ቦታ ለባለስልጣኑ በየጊዜው ማሳወቅ የሚችል መሆኑ ሲረጋገጥ፣

ለ) መሳሪያው በግብይት ወቅት የግብይቱን ትክክለኛ ቦታ መመዝገብና በደረሰኝ ምዝገባ መልዕክት አካቶ መላክ መቻሉ ሲረጋገጥ፣

d) Where it is verified that the Sales Registration System grants access to services only through a username and password or other authorized authentication methods;

4 Where the Sales Registration System has the capability to operate in an offline mode, it shall fulfill the following requirements:

a) Where it is verified through testing that the system has implemented the Offline Resiliency Specification prepared by the Authority;

b) Where it is verified that the system is capable of transmitting and registering transaction data performed offline as soon as the real-time connection, which was interrupted for various reasons, is restored;

c) Notwithstanding the provisions set forth under letters 'A' and 'B' above, the business sectors for which this offline requirement is mandatory are attached as an annex to this directive.

5 Where the Sales Registration System is installed and operates on Mobile Point of Sale (mPOS) terminals, mobile phones, or other modern mobile devices:

a) Where it is verified that the device is capable of periodically reporting its Geo-location to the Authority;

b) Where it is verified that the device is capable of recording the exact Geo-location of the transaction at the time of sale

and including this data within the receipt registration message;

ሐ) መሳሪያው በተፈቀደለት የስራ አካባቢ ብቻ የሚሰራ መሆኑ ሲረጋገጥ

c) Where it is verified that the device operates only within the authorized Geo-fenced work area;

6/ የሽያጭ መመዝገቢያ ስርዓቱ በባለስልጣኑ የኤሌክትሮኒክ ደረሰኝ መመዝገቢያ ሥርዓት ከታች የተገለጹትን የደህንነት ማረጋገጫ ሂደቶች ማሟላት ይኖርበታል።

ሀ) ከኢንፎርሜሽን መረብ ደህንነት አስተዳደር የሶፍትዌር ደህንነት ማረጋገጫ ሰርተፊኬት ሲያቀርብ፣

ለ) ኤሌክትሮኒክ ደረሰኝ መመዝገቢያ ሥርዓቱ ውስጥ የተተገበሩ የማንነት ማረጋገጫ፣ የግንኙነት መመስጠሪያ እና ሌሎች የደህንነት አሰራሮችን መተግበሩ ሲረጋገጥ፣

ሐ) በዲጂታል ፊርማ የተረጋገጠ ግንኙነትና የመረጃ መላላክን ማስቻሉ ሲረጋገጥ፣

6 The Sales Registration System shall ensure fulfillment of the security authentication processes of the Authority's Electronic Receipt Registration System as specified below:

a) Where a software security clearance certificate is presented from the Information Network Security Administration (INSA);

b) Where it is verified that the authentication, communication encryption, and other security procedures implemented within the Electronic Receipt Registration System have been applied;

c) Where it is verified that the system enables communication and data exchange secured by digital signatures;

5. የሽያጭ መመዝገቢያ ሶፍትዌር አገልግሎት ፈቃድ አሰጣጥ

1/ የሽያጭ መመዝገቢያ ስርዓቱ በዚህ መመሪያ በአንቀጽ 4 ከንዑስ አንቀጽ 1 እስከ 3 እና 6 የተገለጹትን መስፈርቶች ሙሉ በሙሉ አሟልቶ ሲገኝ፣

2/ የሽያጭ መመዝገቢያ ስርዓቱ የተጠቃሚ ታክስ ከፋዮችን መረጃ ደህንነቱ ተጠብቆና

5. Licensing of Sales Registration Software as a Service (SaaS)

1 Where the Sales Registration System is found to be in full compliance with the requirements set forth under Article 4, sub-articles 1 to 3 and 6 of this directive;

2 Where it is verified that the Sales Registration System is capable of

ተለይቶ መያዝ የሚያስችል መሆኑ ሲረጋገጥ እንዲሁም መረጃውን ለማስተዳደርና ለመቆጣጠር የሚያስችል አገልግሎት እንዳለው ሲረጋገጥ፣

3/ ተጠቃሚ ታክስ ከፋዮች በፈለጉ ጊዜ መረጃቸውን ሙሉ በሙሉ ለማውጣት፣ ወደ ሌላ አገልግሎት ሰጪ ለማዛወር እና የተዛወረውን መረጃ ለማጥፋት የሚያስችል መተግበሪያ እንዳለው ሲረጋገጥ፣

4/ ሥርዓቱ ቢያንስ በሁለት የመረጃ ማዕከሎች ዳታ መገልበጥ መቻሉ ሲረጋገጥና በአንደኛው ማእከል ችግር ቢኖር ከሌላ ማዕከል አገልግሎት መስጠት መቻሉ ሲረጋገጥ፣

5/ የግብር ከፋዮች መረጃ ደህንነቱ የተጠበቀ እና ከባለስልጣኑና ከታክስ ከፋዩ ውጪ በሌላ አካል እንደማይገኝ ሲረጋገጥ፣

6/ ከሥርዓቱ ጋር አብሮ የሚሰራ ተንቀሳቃሽ የሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያ ሲኖረው በዚህ መመሪያ በአንቀጽ 4 ንዑስ አንቀጽ 5 ተሟልተው ሲገኙ ነው።

maintaining user taxpayer data securely and in isolation, and it is confirmed that the system possesses the necessary features for data management and control;

3 Where it is verified that the application enables user taxpayers to fully export their data at any time, migrate it to another service provider, and delete the migrated data;

4 Where it is verified that the system is capable of Data Replication across at least two datacenters, and it is confirmed that service continuity is maintained from the second datacenter in the event of a failure in the primary datacenter;

5 Where it is verified that taxpayer data is secure and inaccessible to any party other than the Authority and the taxpayer;

6 Where the system includes mobile sales registration devices, and where the requirements specified under Article 4, sub-article 5 of this directive are found to be fulfilled.

6. በኢኮሜርስ ወይም በዲጂታል ገበያ ቦታ ስለሚሰጥ ደረሰኝ ፈቃድ አሰጣጥ

1/ ኢኮሜርስ ወይም ዲጂታል ገበያ ስርዓት በዚህ መመሪያ በአንቀጽ 4 ከንዑስ አንቀጽ 1 እስከ 3 እና 6 የተገለጹትን መስፈርቶች ሙሉ በሙሉ አሟልቶ ሲገኝ፣

2/ የገበያውን ተጠቃሚ ግብር ከፋዮችን በተናጠል መመዝገብና ለባለስልጣኑ ማሳወቅ ሲችል፣

6. Licensing of invoice issued by E-commerce or Digital Marketplace Platforms

1 Where the E-commerce or Digital Marketplace system is found to be in full compliance with the requirements set forth under Article 4, sub-articles 1 to 3 and 6 of this directive;

2 Where the system is capable of separately registering market-user taxpayers and notifying the Authority;

3/ የገበያው ተጠቃሚ ግብር ከፋዮች እና ኢኮሜርስ ወይም ዲጂታል ገበያ ቦታው ላይ የሚያደርጉት ግንኙነት እና የመረጃ ልውውጥ ደህንነቱ የተጠበቀ መሆኑ ሲረጋገጥ፣

3 Where it is verified that the interaction and data exchange between the market-user taxpayers and the E-commerce or Digital Marketplace are secure;

4/ የገበያውን ተጠቃሚ ግብር ከፋዮች ባለስልጣኑ በተፈለገ ጊዜ ማገድ እና ወደ ሥራ መመለስ የሚያስችል አገልግሎት እንዳለው ሲረጋገጥ፣

4 Where it is verified that the system possesses a feature that enables the Authority to suspend market-user taxpayers and reinstate them as necessary;

5/ በግብይት ወቅት የሚሰጥ ደረሰኝ የሻጭ ወይም የአገልግሎት ሰጪውን መረጃ በትክክል የሚያሳይ ሲሆን፣

5 Where the invoice issued at the time of transaction accurately displays the information of the seller or the service provider;

6/ በአንድ ግብይት በኢኮሜርስ ወይም በዲጂታል ገበያ ቦታ አንቀሳቃሹን ጨምሮ ከአንድ በላይ ሻጮች ወይም አገልግሎት ሰጪዎች በሚኖሩበት ወቅት እያንዳንዳቸው ሻጮች ወይም አገልግሎት ሰጭዎች በተናጠል ለሸያጩ ወይም ለሰጡት አገልግሎት በየራሳቸው ግብር ከፋይ መለያ ቁጥር፣ አድራሻና ስም ደረሰኝ መስጠት የሚያስችል መሆኑ ሲረጋገጥ፣

6 Where it is verified that the system enables each seller or service provider to issue an individual receipt using their own Taxpayer Identification Number (TIN), address, and name, in cases where a single transaction involves multiple sellers or service providers, including the E-commerce or Digital Marketplace operator;

7/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 6 የተገለፀው እንደተጠበቀ ሆኖ ለህትመት ወይም ለአጠቃቀም አመችነት የእያንዳንዱን ደረሰኝ ይዘት በግልፅ የሚያሳይ ሆኖ በአንድ ላይ ሊታተም ወይም ሊታይ ይችላል፣

7 Notwithstanding the provisions of sub-article 6 of this Article, receipts may be printed or displayed together for printing or user convenience, provided that the content of each individual receipt is clearly shown;

7. <u>የሽያጭ መመዝገቢያ ሥርዓት/ሶፍትዌር ፈቃድ አሰጣጥ</u>

7 <u>Licensing of Sales Registration Systems</u>

1/ የሽያጭ መመዝገቢያ ሥርዓት ፈቃድ የሚሰጠው በዚህ መመሪያ በአንቀጽ 4 ከንዑስ አንቀጽ 1 እስከ 3 እና 6 የተገለጹት መስፈርቶች ሙሉ በሙሉ ተሟልተው ሲገኙ ነው።

1 Licensing of a Sales Registration System shall be granted upon full compliance with the requirements set forth under Article 4, sub-articles 1 to 3 and 6 of this directive.

2/ ከቀጥታ ግንኙነት ውጪ የሚሰራ የሽያጭ መመዝገቢያ ሥርዓት ሲሆን፣ በዚህ መመሪያ በአንቀጽ 4 ንዑስ አንቀጽ 4 የተገለጹት መስፈርቶች ተሟልተው ሲገኙ ነው።

3/ የሽያጭ መመዝገቢያ ሥርዓቱ በተንቀሳቃሽ መሣሪያ ላይ የሚሰራ ሲሆን በዚህ መመሪያ በአንቀጽ 4 ንዑስ አንቀጽ 5 ተሟልተው ሲገኙ ነው።

2 In the case of Sales Registration System capable of operating in offline mode, licensing shall be granted where the requirements specified under Article 4, sub-article 4 of this directive are found to be fulfilled.

3 Where the Sales Registration System operates on a mobile device, licensing shall be granted where the requirements specified under Article 4, sub-article 5 of this directive are found to be fulfilled

8. ታክስ ከፋይ ለራሱ ብቻ የሚጠቀምበት የሽያጭ መመዝገቢያ ሥርዓት ፈቃድ አሰጣጥ

1/ ታክስ ከፋዩ ለራሱ ብቻ የሚጠቀምበት ሥርዓት ፈቃድ የሚሰጠው በዚህ መመሪያ በአንቀጽ 4 ከንዑስ አንቀጽ 1 እስከ 3 እና 6 የተገለጹት መስፈርቶች ሙሉ በሙሉ አሟልቶ ሲገኝ ነው።

2/ ከቀጥታ ግንኙነት ውጪ የሚሰራ የሽያጭ መመዝገቢያ ሥርዓት ሲሆን፣ በዚህ መመሪያ በአንቀጽ 4 ንዑስ አንቀጽ 4 የተገለጹት ተሟልተው ሲገኙ ነው።

3/ ከሥርዓቱ ጋር አብሮ የሚሰራ ተንቀሳቃሽ የሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያ ሲኖረው በዚህ መመሪያ በአንቀጽ 4 ንዑስ አንቀጽ 5 የተገለጹት ተሟልተው ሲገኙ ነው።

8. Licensing of a sales registration System for the Taxpayer's Exclusive Use

1 Licensing of a system developed for the taxpayer's exclusive use shall be granted upon full compliance with the requirements set forth under Article 4, sub-articles 1 to 3 and 6 of this directive

2 In the case of Sales Registration System capable of operating in offline mode, licensing shall be granted where the requirements specified under Article 4, sub-article 4 of this directive are found to be fulfilled.

3 Where the system includes mobile sales registration devices, and where the requirements specified under Article 4, sub-article 5 of this directive are found to be fulfilled.

9. የኤሌክትሮኒክ ሽያጭ መመዝገቢያ ሶፍትዌር/ሥርዓት ፍተሻ ቅድመ ሁኔታዎች

ማንኛውም የኤሌክትሮኒክ ሽያጭ መመዝገቢያ ስርዓት በባለሰልጣኑ እንዲፈተሽ ሲቀርብ፦

9. Pre-conditions for Testing Electronic Sales Registration software/System

When any Electronic Sales Registration System is submitted to the Authority for testing:

1/ በተዘጋጀው የሙከራ ሲስተም ላይ ተመዝግቦ በአንቀጽ 4 ንዑስ አንቀጽ 1 የተዘረዘሩትን አገልግሎቶች መስጠት እንደሚችል አረጋጋጭ ሙከራዎችን ማከናወን እና ማለፍ ይኖርበታል።

2/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 የተጠቀሰው ሙከራ መከናወኑን ለማረጋገጥ ለፍተሻ የተጠቀመበት የተመዘገበ ሲስተም መለያ ቁጥር ሙከራው የተደረገበት ጊዜ እና በአቅራቢው የተሞላ የፍተሻ ማሳያ ቅፅ ማቅረብ አለበት።

3/ ከዚህ በታች የተዘረዘሩት የሰነድ ማስረጃዎች መቅረብ ይኖርባቸዋል፤

ሀ) የሽያጭ መመዝገቢያ ሶፍትዌሩ/ስርዓቱ ዝርዝር የአገልግሎት መግለጫ እንዲሁም አገልግሎት አይነት፣

ለ) የሶፍትዌሩ ዲዛይን፣

ሐ) ሶፍትዌሩን/ሥርዓቱን ለማልማት አገልግሎት ላይ የዋሉ ቴክኖሎጂዎች ዝርዝርና ስሪት፣

መ) ሶፍትዌሩን/ሥርዓቱን አገልግሎት ላይ ለማዋል የሚያስፈልግ ቴክኖሎጂና መሳሪያዎች አይነት ዝርዝር፣

ሠ) የሶፍትዌሩ/ሥርዓቱ ስሪት እና መጨረሻ ማሻሻያ የተደረገበት ጊዜ፣

ረ) ሽያጭ መመዝገቢያ ስርዓቱ ከሌሎች አገልግሎቶች ጋር የተጣመረ ወይም ሌላ ዋና ስራ ባለው መሳሪያ ላይ የተጫነ ከሆነ በሁለቱ መካከል ያለውን የመረጃ ቅብብል እና ትስስር በዝርዝር የሚያሳይ ስነድ፣

ሰ) በሽያጭ መመዝገቢያ ስርዓቱ የተካተቱ የደረሰኝ አይነቶች፣ የአገልግሎቶች እና የተጠቃሚ ታክስ ከፋዮች አይነትና የፍላጎት መግለጫ ሰነድ፣

1/ It must undergo and pass verification tests on the testing system to demonstrate its capability to provide the services listed under Article 4, sub-article 1;

2/ To verify that the testing mentioned under sub-article 1 of this Article has been conducted, the system identification number (System Number) used for the inspection, the time of testing, and completed check list must be submitted;

3/ The following supporting documents must be submitted፡

a) A detailed description of the sales registration system's functionalities as well as the types of services it provides;

b) The software design;

c) A list and version of the technologies utilized to develop the system;

d) A list of the technology and equipment required to deploy and operate the system;

e) The system version and the date of its last update;

e) Where the sales registration system is integrated with other services or installed on a device with another primary function, a document showing in detail the data exchange and integration between the two must be submitted;

g) A document specifying the types of invoices included in the sales registration system, the types of services and target taxpayers, and a statement of requirements;

4/ ሽያጭ መመዝገቢያ ስርዓቱ ሙሉ በሙሉ ወይም በከፊል የሶስተኛ ወገን የአእምሯዊ መብት ጥበቃ ያለው ከሆነ ወይም የአእምሯዊ መብት ጥበቃ ባይኖረውም በአቅራቢው ያልበለጸገና ከሌላ ምንጭ ወይም ሌላ የተገኘ ከሆነ በሚቀርቡት ሰነዶች ላይ በግልጽ መጠቀስ ይኖርበታል፤

4/ Where the sales registration system or any of its components are subject to third-party intellectual property rights, or if it is obtained from other sources (such as Open Source or others) despite not having intellectual property protection and was not developed by the supplier, this must be clearly stated in the submitted documents;

10. <u>የኤሌክትሮኒክ የሽያጭ መመዝገቢያ ሥርዓት የፍተሻ ሂደት</u>

10. <u>Electronic Sales Registration System Inspection Process</u>

የኤሌክትሮኒክ የሽያጭ መመዝገቢያ ሥርዓት በባለሰልጣኑ እንዲፈተሽ ሲቀርብ የሚከተሉት ሂደቶች መከናወን አለባቸው፤

When an Electronic Sales Registration System is submitted to the Authority for testing, the following procedures shall be carried out

1/ ለፍተሻ የሚያስፈልጉና በዚህ መመሪያ አንቀጽ 9 የተዘረዘሩ ሰነዶች ተሟልተው ለፍተሻ ቡድኑ መቅረብ ይኖርባቸዋል፣

1/ The documents required for inspection as listed under Article 9 of this Directive must be fully compiled and submitted to the inspection team;

2/ የፍተሻ ቡድኑ የቀረቡ ሰነዶችን በመገምገም ያልተሟሉ ወይም ተጨማሪ አስረጅ ሰነዶችን ሊጠይቅ ይችላል፣

2) The inspection team may, upon reviewing the submitted documents, request incomplete documents or additional explanatory documents;

3/ የፍተሻ ቡድኑ እንዳስፈላጊነቱ የሽያጭ መመዝገቢያ ሥርዓት አቅራቢውን ስለስርዓቱ ተጨማሪ ማብራሪያ እንዲሰጥና እንዲያሳይ ሊጠይቅ ይችላል።

3) The inspection team may, as necessary, require the sales registration system supplier to provide further explanations and demonstrate the system's operations.

4) አቅራቢው የፍተሻ ቡድኑ ለፍተሻ ዝግጁ ሲሆን ለፍተሻ የሚያስፈልጉ ናሙና የሽያጭ መመዝገቢያ ስርዓቱ የተጫነበት ኮምፒውተር ወይም መሳሪያ ማቅረብ ይኖርበታል፣

4) The supplier must provide a sample computer or device with the sales registration system installed when the inspection team is ready to conduct the inspection;

5) ለፍተሻ የቀረበ ሥርዓት ፍተሻው ከተጀመረ በኋላ እና ሳይጠናቀቅ በፍተሻ

5) No modifications may be made to a system submitted for inspection

በተገኙ ጉድለቶች ወይም በሌላ ምክንያት በቀረበው ሥርዓት ላይ ማሻሻያ ማድረግ አይቻልም፤

6) በፍተሻ ወቅት የሽያጭ መመዝገቢያ ስርዓቱ በመስፈርቱ መሰረት ትክክለኛ መጠየቂያ ካልላከ፣ ካልተቀበለ ወይም የፍተሻ ቡድኑ የተሰማማበት ጉድለት ከተለየ፤ ጉድለቱ ተሰተካክሎ ፍተሻው በአዲስ መልክ መጀመር ይኖርበታል።

7) ለፍተሻ የቀረበ ሶፍትዌር ሁሉንም የሚመዘንባቸውን መስፈርቶች ሙሉ በሙሉ እና ያለምንም ግድፈት ማሟላት ይኖርበታል።

8) አንድ እውቅና ለማግኘት ለፍተሻ የቀረበ የሽያጭ መመዝገቢያ ሥርዓት በፍተሻ ወቅት ጉድለት ከተገኘበት ማስተካካያ በማድረግ እንደገና ማስፈተሽ የሚችለው በስድስት ወር ጊዜ ውስጥ ለሶስት ጊዜ ብቻ ነው።

9) የሽያጭ መመዝገቢያ ሶፍትዌሩ እንደአገልግሎቱ አይነት የሚደረገውን ፍተሻ በትክክል ሲያልፍና ሲጸድቅ የሲስተሙ ልዩ መለያ እና ስሪት ተመዝግቦ የሶፍትዌሩ ብቃት ማረጋገጫ ለአስፈተሸው አካል ይሰጣል።

once the inspection process has commenced and before its completion, whether due to defects identified during testing or for any other reason;

6) If, during the inspection, the sales registration system fails to send or receive accurate requests in accordance with the standards, or if a defect agreed upon by the inspection team is identified, the defect must be rectified and the inspection process must be restarted as a new.

7) Any software submitted for inspection must fully and without any deficiency meet all the evaluation criteria set forth.

8) Where a sales register system submitted for certification is found to have defects during inspection, it may be re-inspected after rectification for a maximum of three times only within a period of six months.

9) Upon the successful completion and approval of the inspection of the sales registration software based on the type of service, the system's checksum and version shall be recorded, and a software competency certificate shall be issued to the inspecting entity.

11. ፈቃድ የተሰጠውን የኤሌክትሮኒክ የሽያጭ መመዝገቢያ ሶፍትዌርን/ሥርዓትን ስለማሻሻል

ፈቃድ የተሰጠውን የኤሌክትሮኒክ የሽያጭ መመዝገቢያ ሥርዓትን ለማሻሻል እና በሥራ ላይ ለማዋል የሚከተሉት ሊፈጸሙ ይገባል፤

11. Modification of a Licensed Electronic Sales Registration System

In order to upgrade and implement an authorized Electronic Sales Registration System, the following requirements must be fulfilled:

1/ ማንኛውንም ተፈትሾ ፈቃድ የተሰጠው የኤሌክትሮኒክ ሽያጭ መመዝገቢያ ሥርዓት ከባለስልጣኑ እውቅና ወጪ አሻሽሎ ስራ ላይ ማዋል አይቻልም፣

1/ No licensed electronic sales registration system may be modified and implemented without the prior recognition and approval of the Authority,

2) ፈቃድ የተሰጠው የኤሌክትሮኒክ ሽያጭ መመዝገቢያ ሥርዓት ማሻሻያ ማድረግ በሚያስፈልግበት ጊዜ አቅራቢው የለውጡን ዝርዝር መረጃ፣ ለውጡ ያስፈለገበትን ምክንያት እና የለውጡን ተጽዕኖ እንዲሁም የተለወጠውን ሶፍትዌር ልዩ መለያ ፣ ስሪት እና ቀን በመጥቀስ ለባለስልጣኑ ማሳወቅ አለበት፣

2) When a licensed electronic sales registration system requires modification, the supplier must notify the Authority by specifying the details of the change, the reason for the change, its impact, and the modified software's unique identifier (Checksum), version, and date,

3/ ባለስልጣኑ የቀረበውን የማሻሻያ ጥያቄ በመተንተንና የለውጡን ደረጃ በመለየት በሽያጭና ደረሰኝ አሰጣጥ ሂደት ቀጥተኛ ተጽእኖ የሌላቸውን ማሻሻያዎች ብቻ ሊፈቅድና ስራ ላይ እንዲውል ሊያደርግ ይችላል፣

3/ The Authority, after analyzing the modification request and determining the level of the change, may approve and allow the implementation of only those modifications that do not have a direct impact on the sales and receipt issuance process,

4/ ባለስልጣኑ የቀረበውን የማሻሻያ ጥያቄ በመተንተንና የለውጡን ደረጃ በመለየት በሽያጭና ደረሰኝ አሰጣጥ ሂደት ቀጥተኛ ተጽእኖ ባላቸው እንደ የደህንነት፣ የታክስ ስሌት፣ የመልዕክት ልውውጥ እና ተዛማጅ አገልግሎቶች ላይ ሲሆን በአንቀጽ 9 እና 10 በቀረበው መሰረት የማሻሻያ ለውጥ ፍተሻ በማድረግ ማለፋቸው ሲረጋገጥ ስራ ላይ እንዲውል ፈቃድ ይሰጣል።

4/ Where the Authority, after analyzing the modification request and determining the level of the change, identifies that the modification has a direct impact on the sales and invoice issuance process—such as security, tax calculation, messaging, and related services—it shall grant approval for implementation only after conducting a Regression Test in accordance with Articles 9 and 10 and ensuring the system's compliance

12. <u>የኤሌክትሮኒክ የሽያጭ መመዝገቢያ ሶፍትዌር/ሥርዓት ፈቃድ እድሳት</u>

12 <u>Renewal of Electronic Sales Registration System License</u>

ተፈትሾ ፈቃድ የተሰጠው የኤሌክትሮኒክ የሽያጭ መመዝገቢያ ሥርዓት የፈቃድ እድሳት ሲደረግ የሚከተሉት ተግባራዊ ሊሆኑ ይገባል፤

The following shall be implemented during the renewal of a licensed electronic sales registration system፡

1/ ማንኛውም ተፈትሾ ፈቃድ የተሰጠው የኤሌክትሮኒክ ሽያጭ መመዝገቢያ ሥርዓት በየሁለት ዓመቱ ፈቃዱ ሊታደስ ይገባል፤

2) ለእድሳት በሚቀርብበት ወቅት፤

ሀ) ከኢንፎርሜሽን መረብ ደህንነት አስተዳደር የተሰጠ አንድ ወር ያልበለጠው የሶፍትዌር ደህንነት ማረጋገጫ ሰርተፊኬት፣

ለ) በባለስልጣኑ የተሰጡ ማሻሻያዎች በጊዜ ገደባቸው ውስጥ ስለመተግበራቸው የሚገልጽ ማረጋገጫ፣

3/ እውቅና በተሰጠው ሶፍትዌር ላይ ያለባለስልጣኑ እውቅና ማሻሻያ እንዳልተደረገበት የሚያረጋግጥ የተመዘገበ የሲስተም መለያ መቅረብ አለበት።

4/ ባለስልጣኑ እንደ አስፈላጊነቱ በኤሌክትሮኒክ ሽያጭ መመዝገቢያ ሥርዓቱ ላይ የእድሳት ፍተሻዎችን ያደርጋል።

5/ የእድሳት ጊዜ ካለፈ ከአስር ቀን በኋላ የኤሌክትሮኒክ ሽያጭ መመዝገቢያ ሥርዓቱ ለገበያ እንዳይቀርብ ይታገዳል።

6/ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 5 የተገለጸው የእድሳት ጊዜ ያለፈው የኤሌክትሮኒክ ሽያጭ መመዝገቢያ ሥርዓት እንደ አዲስ መፈተሽና እውቅና ማግኘት አለበት።

1/ Any licensed electronic sales registration system that has been inspected and approved must undergo a license renewal every two years,

2) Upon applying for license renewal

a) A software security assurance certificate issued by the Information Network Security Administration (INSA) that is not more than one month old,

b) Verification confirming that modifications issued by the Authority have been implemented within the specified timeframe

3/ A registered system checksum must be presented to verify that no modifications have been made to the authorized software without the Authority's approval.

4/ The Authority shall, as necessary, conduct renewal inspections on the electronic sales registration system.

5/ The electronic sales registration system shall be suspended from the market if ten days have elapsed since the expiry of the renewal period.

6/ The elapse of 10 days after the renewal period stated in sub article 5 of this article, an electronic sales registration system must undergo a new inspection and obtain authorization.

13. ፈቃድ የተሰጠው የኤሌክትሮኒክ የሽያጭ መመዝገቢያ ሥርዓት ስረዛ

ፈቃድ የተሰጠው የኤሌክትሮኒክ የሽያጭ መመዝገቢያ ሥርዓት በሚከተሉት ምክንያቶች ፈቃዱ ሊሰረዝ ይችላል፤

1/ ባለስልጣኑ ያወጣቸውን ማሻሻያዎች በተሰጠው የጊዜ ገደብ ሳይተገበር ሲቀር፣

2/ የኤሌክትሮኒክ ሽያጭ መመዝገቢያ ሥርዓቱ የእድሳት ጊዜ ከሦስት ወር በላይ ካለፈ፤

3/ ለኤሌክትሮኒክ ሽያጭ መመዝገቢያ ሥርዓቱ የተሰጠው ደህንነት ማረጋገጫ ሲሰረዝ ወይም ጊዜው ሲያልፍ፣

4/ የኤሌክትሮኒክ ሽያጭ መመዝገቢያ ሥርዓቱ ጥቅም ላይ ውሎ በተጠቃሚዎች ወይም በባለስልጣኑ ጉድለት ከተገኘበትና በተሰጠው ጊዜ ውስጥ ማስተካከያ ካልተደረገበት፣

5/ ፈቃድ ከተሰጠው በኋላ በኤሌክትሮኒክ ሽያጭ መመዝገቢያ ሥርዓቱ ላይ ከባለስልጣኑ ዕውቅና ውጪ ተለውጦ ወይም ማሻሻያ በማድረግ በስራ ላይ ውሎ ከተገኘ፣

6/ የግብይት መረጃን በህግ ከተፈቀደው ውጭ ለሶስተኛ አካል ካጋራ ወይም ለሌላ አገልግሎት ተጠቅሞ ከተገኘ

13. Cancellation of Licensed Electronic Sales Registration System

The license of an authorized electronic sales registration system may be revoked for the following reasons፡

1/ Failure to implement modifications issued by the Authority within the specified timeframe;

2/ when the renewal period of the electronic sales registration system has overdue for more than three months;

3/ When the security assurance certificate issued for the electronic sales registration system is revoked or expires;

4/ when the electronic sales registration system, while in use, is found to have defects by users or the Authority and such defects are not rectified within the specified timeframe;

5/ when the electronic sales registration system is found to be in operation after having been altered or modified without the Authority's approval;

6/ when it is found that transaction data has been shared with a third party outside of legal authorization or has been used for other purposes;

ክፍል ሦስት

የአቅራቢዎችና አገልግሎት ሰጪዎች እውቅና አሰጣጥና አደረጃጀት

SECTION THREE

Accreditation and Organizational Requirements for Suppliers and Service Providers

14. የኤሌክትሮኒክ የሽያጭ መመዝገቢያ ሥርዓት አቅራቢዎች እና አገልግሎት ሰጪዎች ዕውቅና ምስክር ወረቀት አሰጣጥ

የሽያጭ መመዝገቢያ ሥርዓት አቅራቢዎች እና አገልግሎት ሰጪዎች የዕውቅና ምስክር ወረቀት ለመስጠት የሚከተሉት ሊፈጸሙ ይገባል፤

1/ የሽያጭ መመዝገቢያ ሥርዓት አቅራቢነት ወይም አገልግሎት ሰጪነት የሚያመለክት ሰው ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን መስፈርቶች ማሟላት ይኖርበታል፤

ሀ) በኢትዮጵያ የተመዘገበ ህጋዊ የንግድ ፈቃድ ያለው ሰው፣

ለ) የንግድ ዘርፉ በሶፍትዌር ማልማት፣ ማማከር ወይም መሰል አገልግሎት አቅራቢነት የተሰማራ፣

ሐ) ፈቃድ የተሰጠውን ሶፍትዌር ለማደስና ለማዘመን የሚያስችል መብት እንዳለው ማረጋገጫ የሚያቀርብ፣

መ) በሚያቀርበው የሽያጭ መመዝገቢያ ሥርዓት አይነት በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 6 የተዘረዘሩት በኢትዮጵያ እውቅና ካለው የትምህርት ተቋም በኮምፒውተር ሳይንስ፣ በሶፍትዌር ልማትና ተዛማጅ ዘርፎች ቢያንስ በዲግሪ የተመረቁ፣ የተረጋገጠ የትምህርት ማስረጃ ሰነድ ማቅረብ የሚችሉና በዘርፉ ቢያንስ ሁለት አመት የስራ ልምድ ያላቸው የድጋፍ ሰጪ

14. Issuance of Accreditation Certificate for Electronic Sales Registration System Suppliers and Service Providers

The following conditions shall be met to issue an accreditation certificate for electronic sales registration system suppliers and service providers

1/ Any person applying to be a supplier or service provider of an electronic sales registration system shall fulfill the following requirements

a) A person having a valid business license registered in Ethiopia;

b) Engaged in a business sector specialized in software development, consultancy, or related service provision;

c) Providing confirmation of the legal right to renew and update the authorized software;

d) Depending on the type of sales registration system, having support professionals as specified under Sub-Article 6 of this Article who are graduates with at least a degree in Computer Science, Software Engineering, or related fields from a recognized Ethiopian educational institution, capable of providing authenticated

ባለሙያዎች ሲኖሩትና ለዚህም ማስረጃ ማቅረብ የሚችል፣

ሠ) ለተጠቃሚ ታክስ ከፋዮች በድረ-ገጽ እና በስልክ አገልግሎት የሚሰጥ የተደራጀ የድጋፍ ማዕከል ያለው፣

2/ ለሽያጭ መመዝገቢያ ስርዓት አቅራቢነት ስለሚሰጥ ማረጋገጫ ፤

ሀ) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 የተጠቀሱትን መስፈርቶች ሙሉ በሙሉ ሲያሟላ፣

ለ) በአንቀጽ 4 የተቀመጡትን መስፈርቶች ሙሉ በሙሉ የሚያሟላና ተፈትሾ እውቅና የተሰጠው አቅራቢ ቢያንስ አንድ የኤሌክትሮኒክ ሽያጭ መመዝገቢያ ስርዓት ያለው፣

ሐ) አቅራቢው በሚኖሩት ተጠቃሚ ታክስ ከፋዮች ብዛት እና በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 6 መሰረት የባለሙያዎች ብዛት የሚወሰን ሆኖ ፈቃድ በሚጠይቅበት ወቅት መስፈርቱን የሚያሟሉ ቢያንስ 4 ባለሙያዎች ያሉት፣

መ) አቅራቢው በሚኖሩት ተጠቃሚ ታክስ ከፋዮች ብዛት ወይም በታክስ ከፋዮች አመታዊ ጥቅል ሽያጭ መጠንን መሰረት በማድረግ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀጽ 6 መሰረት የሚታሰብ ሆኖ ፈቃድ በሚጠይቅበት ወቅት በየሁለት አመቱ የሚታደስ በባንክ ወይም በመድን የተረጋገጠ 30,000 (ሰላሳ ሺህ) የአሜሪካን ዶላር የመልካም አፈጻጸም ዋስትና ማቅረብ ይኖርበታል፣

educational credentials and having at least two years of work experience in the field, and being able to provide evidence for the same;

e) Possessing an organized support center that provides services to user taxpayers via website and telephone;

2/ For accreditation as a Sales Registration System Supplier

a) Upon full compliance with the requirements specified under Sub-Article 1 of this Article;

b) Having at least one electronic sales registration system that fully meets the requirements set out under Article 4 and has been inspected and accredited;

c) Having at least 4 qualified professionals at the time of application for accreditation, provided that the total number of professionals shall be determined based on the number of user taxpayers and in accordance with Sub-Article 6 of this Article;

d) At the time of application for accreditation, the applicant shall provide a performance guarantee of 30,000 (Thirty Thousand) USD secured by a bank or insurance and renewable every two years; the specific amount of the guarantee shall be calculated based on the number of user taxpayers or their annual aggregate sales volume in accordance with Sub-Article 6 of this Article.

3/ የሽያጭ መመዝገቢያ ሶፍትዌር/ሥርዓት አገልግሎት አቅራቢነት ስለሚሰጥ ማረጋገጫ፤

ሀ) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 የተጠቀሱትን ሙሉ በሙሉ ሲያሟላ፣

ለ) በአንቀጽ 4 እና 5 የተቀመጡትን መስፈርቶች ሙሉ በሙሉ የሚያሟላና ተፈትሾ እውቅና የተሰጠው ቢያንስ አንድ የኤሌክትሮኒክ ሽያጭ መመዝገቢያ አገልግሎት ስርዓት ያለው፣

ሐ) በሚኖሩት ተጠቃሚ ግብር ከፋዮች ብዛት እና በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 6 መሰረት የባለሙያዎች ብዛት የሚወሰን ሆኖ ፈቃድ በሚጠይቅበት ወቅት መስፈርቱን የሚያሟሉ ቢያንስ 6 ባለሙያዎች ያሉት፣

መ) በሚኖሩት በተጠቃሚ ታክስ ከፋዮች ብዛት ወይም ታክስ ከፋዮቻቸው አመታዊ ጥቅል ሽያጭ መጠን መሰረት በማድረግ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀጽ 6 መሰረት የሚወሰን ሆኖ ፈቃድ በሚጠይቅበት ወቅት በየሁለት አመቱ የሚታደስ በባንክ ወይም በመድን የተረጋገጠ 50,000 (ሀምሳ ሺህ) የአሜሪካን ዶላር የመልካም አፈጻጸም ዋስትና ማቅረብ ይኖርበታል፣

ሠ) ተጠቃሚ ታክስ ከፋዮች ሌላ የሽያጭ መመዝገቢያ ሥርዓት ለመጠቀም ወይም በሌላ ምክንያት መረጃቸውን ማዛወር በፈለጉ ጊዜ መረጃቸውን እንዲያወጡ፣ ወደሌላ እንዲያዛውሩ እና እንዲያጠፉ የሚያስችል አገልግሎት ሊኖረው ይገባል።

3/ For accreditation as a Sales Registration software/System as a Service Provider;

a) Upon full compliance with the requirements specified under Sub-Article 1 of this Article;

b) Having at least one electronic sales registration service system that fully meets the requirements set out under Articles 4 and 5 and has been inspected and accredited;

c) Having at least 6 qualified professionals at the time of application for accreditation, provided that the total number of professionals shall be determined based on the number of user taxpayers and in accordance with Sub-Article 6 of this Article;

d) At the time of application for accreditation, the applicant shall provide a performance guarantee of 50,000 (Fifty Thousand) USD secured by a bank or insurance and renewable every two years; the specific amount of the guarantee shall be calculated based on the number of user taxpayers or their annual aggregate sales volume in accordance with Sub-Article 6 of this Article.

e) The system shall have a service that enables taxpayers to extract, transfer, and delete their data whenever they wish to use another sales register system or for any other reason.

ረ) ከባለስልጣኑ በተጠየቀ ጊዜ መረጃ ለባለስልጣኑ መስጠት ወይም ለመጠቀም የሚያስችል አገልግሎት ያለው፣

ሰ) አገልግሎቱ የሚቀርብበት መሰረተ ልማት የሚከተሉትን መስፈርቶች ማሟላት ይኖርበታል፣

(1) በአገር ውስጥ የሚገኝ፣

(2) የመረጃ ማዕከሉ ደረጃ ሦስት ዲዛይን ያሟላ ሆኖ በአቅራቢው ወይም በኪራይ የሚገኝ ሊሆን ይችላል፣

(3) ከኤሌክትሮኒክስ ደረሰኝ መመዝገቢያ ስርዓት ጋር በቀጥታ የሚያገናኝ አስተማማኝና መጠባበቂያ ያለው የመረጃ ግንኙነት ያለው መሆን ይኖርበታል፣

(4) የታወቁ ይፋዊ የበይነ መረብ አድራሻዎች ያሉት፣

(5) በቂ የመረጃ ማስተላለፊያ አቅም ያለው የኢንተርኔት አገልግሎት፣

(6) ከአንድ በላይ በሆኑ መረጃ ማዕከላት አገልግሎት ማቅረብ እና አስፈላጊ ሲሆን ከዋናው ማዕከል ውጪ አገልግሎት መስጠት የሚያስችል አቅም ያለው፣

(7) መሰረተ ልማቱ የመረጃ ቴክኖሎጂ ደህንነት ደረጃ እንደሚያሟላ ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት የሚያቀርብ፣

f) Providing a service that enables the provision of information to the Authority or allows the Authority to access and use information upon request;

g) The infrastructure through which the service is provided shall meet the following requirements: -

(1) Being situated within Ethiopia

(2) The data center shall meet the Tier III or Level 3 design standards and may be owned by the provider or obtained through a lease;

(3) A reliable and redundant data communication link that directly connects with the Electronic Invoice Registration System;

(4) Having registered Public IP Addresses;

(5) Internet service with sufficient data transmission bandwidth;

(6) Capable of providing services through more than one data center and ensuring service continuity redundant facility when necessary;

(7) Providing a certificate of assurance confirming that the infrastructure meets Information Technology Security Standards;

4/ ኢኮሜርስ ወይም ዲጂታል ገበያ ቦታ አንቀሳቃሽ የሽያጭ ደረሰኝ ሶፍትዌር/ስርዓት ፈቃድ አሰጣጥ፤

ሀ) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 የተጠቀሱትን ሙሉ በሙሉ ሲያሟላ፣

ለ) በአንቀጽ 4 እና 7 የተቀመጡትን መስፈርቶች ሙሉ በሙሉ የሚያሟላና ተፈትሾ እውቅና የተሰጠው ቢያንስ አንድ ኢኮሜርስ ወይም ዲጂታል ገበያ ቦታ ያለው፣

ሐ) በሚኖረው ዓመታዊ የተጠቃሚ ታክስ ከፋዮች አጠቃላይ የሽያጭ መጠን መሰረት በማድረግ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 6 መሰረት የሚወሰን ሆኖ ፈቃድ በሚጠይቅበት ወቅት በየሁለት አመቱ የሚታደስ በባንክ ወይም በመድን የተረጋገጠ 25,000 (ሃያ አምስት ሺህ) የአሜሪካን ዶላር የመልካም አፈጻጸም ዋስትና ማቅረብ ይኖርበታል፣

መ) በባለስልጣኑ በተጠየቀ ጊዜ መረጃ መስጠት ወይም እንዲጠቀም የሚያስችል አገልግሎት ያለው፣

5/ ታክስ ከፋዩ ለራሱ ብቻ የሚጠቀምበት የኤሌክትሮኒክስ የሽያጭ መመዝገቢያ ሥርዓት/ሶፍትዌር ፈቃድ አሰጣጥ፤

ታክስ ከፋዩ ለራሱ ብቻ የሚጠቀምበት የኤሌክትሮኒክስ የሽያጭ መመዝገቢያ ሥርዓት ለመፍቀድ የሚከተሉት መስፈርቶች ሊሟላ ይገባል።

4/ Licensing of E-commerce or Digital Marketplace Operators sales Invoice/receipt software/system

a) Fully meeting the requirements specified under Sub-Article 1 of this Article;

b) Having at least one e-commerce or digital marketplace platform that fully meets the requirements set out under Articles 4 and 7 and has been inspected and accredited;

c) At the time of application for accreditation, the applicant shall provide a performance guarantee of 25,000(Twenty Five Thousand) USD secured by a bank or insurance and renewable every two years; the specific amount of the guarantee shall be calculated based on the number of user taxpayers or their annual aggregate sales volume in accordance with Sub-Article 6 of this Article.

d) Providing a service that enables the provision of information to the Authority or allows the Authority to access and use information upon request

5/ Licensing of Electronic Sales Register software/System for the taxpayer's own exclusive use

The following requirements shall be met for the licensing of an Electronic Sales Register

System intended for the taxpayer's own exclusive use፡

ሀ) የታክስ ከፋዩ የስራ ሁኔታ እውቅና ባላቸው አቅራቢዎች በሚያቀርቡት የኤሌክትሮኒክ ሽያጭ መመዝገቢያ ስርዓቶች በበቂ ሁኔታ ሊሸፈን የማይችል ሲሆን፣

a) Where the nature of the taxpayer's business operations cannot be adequately covered by the electronic sales register systems provided by accredited suppliers;

ለ) በዚህ መመሪያ በአንቀጽ 4 ንዑስ አንቀጽ ከ1 እስከ 3 እና 6 የተቀመጡትን መስፈርቶች የሚያሟላና ተፈትሾ እውቅና የተሰጠው የኤሌክትሮኒክ ሽያጭ መመዝገቢያ ሥርዓት ሲኖረው፣

b) Having an electronic sales register system that fully meets the requirements set out under Sub-Articles 1 to 3 and 6 of Article 4 of this Directive, and which has been inspected and accredited;

ሐ) ታክስ ከፋዩ በግልፅ የተለየ ባለቤትና የስራ አመራር አደረጃጀት ያለው ወይም በስራ አመራር ቦርድ የሚተዳደር ሲሆን፣

c) Where the taxpayer has a clearly defined and distinct ownership and management structure, or is administered by a Board of Management;

መ) የታክስ ከፋዩ የሂሳብ መዝግብ አያያዝና አሰራር እውቅና ያለውና ለኦዲት አመች መሆኑ የተረጋገጠ፣

d) Where it is verified that the taxpayer follows standard accounting records and procedures that are convenient for audit purposes;

ሠ) የኤሌክትሮኒክስ የሽያጭ መመዝገቢያ ስርዓቱን በውሰጥ አቅሙ ካለማው ወይም ካልሚው ጋር የጥገናና ድጋፍ ስምምነት ውል ካለው፣

e) Where the taxpayer has developed the electronic sales register system in-house or has entered into a maintenance and support agreement with the developer of the system;

ረ) የኤሌክትሮኒክ የሽያጭ መመዝገቢያ ስርዓቱን ወይም የኤሌክትሮኒክ የሽያጭ መመዝገቢያ ስርዓቱን የተካተተበትን ሶፍትዌር/ስርዓት ለራሱ አገልግሎት ብቻ የሚጠቀም፣

f) Using the electronic sales register system or the software/system in which the electronic sales register system is integrated, exclusively for own use;

ሰ) በሚኖረው ዓመታዊ ጥቅል የሽያጭ መጠን መሰረት በማድረግ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀጽ 6 መሰረት የሚታሰብ ሆኖ ፈቃድ በሚጠይቅበት ወቅት በየሁለት አመቱ የሚታደስ በባንክ ወይም በመድን የተረጋገጠ 15,000 (አስራ አምስት ሽህ) የአሜሪካን ዶላር የመልካም አፈጻጸም ዋስትና ማቅረብ ይኖርበታል፣

g) At the time of application for accreditation, the applicant shall provide a performance guarantee of 15,000 (Fifteen Thousand) USD secured by a bank or insurance and renewable every two years; the specific amount of the guarantee shall be calculated based on the taxpayer’s annual sales volume in accordance with Sub-Article 6 of this Article.

6/ የመልካም አፈጻጸም ዋስትና አቀራረብ እና የባለሙያ ብዛት

ሀ) አቅራቢዎች በተጠቃሚ ታክስ ከፋዮቻቸው ብዛት ወይም ታክስ ከፋዮቻቸው አመታዊ ጥቅል ሽያጭ መጠን መሰረት ከሁለቱ ቀድሞ በተሟላው እንደ አቅራቢነት አይነት ፈቃድ በሚጠይቅበት ወቅት ከተቀመጠው የባለሙያና የመልካም አፈፃፀም ዋስትና በተጨማሪ ከዚህ በታች በቀረበው ሰንጠረዥ ምድብ መሰረት ማቅረብ ይኖርባቸዋል።

6/ Performance Guarantee and Number of Professionals

a) Suppliers shall, in addition to the initial number of professionals and performance guarantee requirements set for their respective supplier category, provide additional requirements based on the number of their user taxpayers or the annual aggregate sales volume of their user taxpayers, whichever is reached first, in accordance with the levels specified in the table below.

ምድብ/ Level	የታክስ ከፋዮች ብዛት /Number of taxpayers	አመታዊ ጥቅል የሽያጭ መጠን / Aggregated Annual Sales (በቢሊዮን ብር/ In Billion Birr)	የባለሙያ ብዛት /Number of Professionals	ዋስትና በአሜሪካን ዶላር/ Guarantee in USD
1	እስከ/Up to 500	እስከ/ up to 5	-	-
2	501 - 2,500	ከ5 በላይ/above - 15	2	10,000
3	2,501 - 5,000	ከ15 በላይ/above - 30	4	20,000
4	5,001 - 8,000	ከ30 በላይ/above - 60	5	30,000
5	8,001 - 12,000	ከ60 በላይ/above - 120	5	50,000
6	12,001 - 17,000	ከ120 በላይ/above - 220	6	70,000
7	17,001 - 23,000	ከ220 በላይ/above - 400	6	100,000
8	23,001 - 30,000	ከ400 በላይ/above - 720	6	150,000
9	30,001 - 40,000	ከ720 በላይ/above - 1,000	8	200,000
10	ከ40,000 በላይ/above	ከ1,000 በላይ/above	8	250,000

ለ) አቅራቢው ተጠቃሚ ታክስ ከፋዮቹ ቁጥር ወይም ዓመታዊ ጥቅል የሽያጫቸው መጠን በማደግ ወይም በመቀነስ በዚህ አንቀጽ በንዑስ አንቀፅ 6 (ሀ) በቀረበው ሰንጠረዥ መሰረት ደረጃ ሲቀይር ተከታትለው ለባለስልጣኑ ማሳወቅ እና በዚሁ የተጠቀሰውን የዋስትና መጠን ማስያዝ እና ባለሙያ ማሟላት አለባቸው፣

b) Where a supplier's level changes—due to an increase or decrease in the number of user taxpayers or their annual aggregate sales volume—in accordance with the table provided under Sub-Article 6(a) of this Article, the supplier shall monitor such changes, notify the Authority accordingly, deposit the specified guarantee amount, and fulfill the required professional staffing;

ሐ) ለራሱ ብቻ የሚጠቀምበት የኤሌክትሮኒክ የሽያጭ መመዝገቢያ ሥርዓት ፈቃድ የተሰጠው ታክስ ከፋይ ዓመታዊ ጥቅል የሽያጩ መጠን በማደግ ወይም በመቀነስ በዚህ አንቀጽ በንዑስ አንቀፅ 6 (ሀ) በቀረበው ሰንጠረዥ መሰረት ምድብ ሲቀይር ተከታትሎ

c) A taxpayer licensed to use an electronic sales register system for own exclusive use shall, where its level changes due to an increase or decrease in the annual aggregate sales volume in accordance with the table provided under Sub-Article 6(a) of this Article, monitor such changes, notify the

ለባለስልጣኑ ማሳወቅ እና በዚሁ ንዑስ አንቀፅ የተጠቀሰውን የዋስትና መጠን ማስያዝ ይኖርበታል፣

Authority accordingly, and deposit the specified guarantee amount;

መ) ከአንድ በላይ ፈቃድ ያለውና በስራ ላይ የዋለ የሽያጭ መመዝገቢያ ስርዓት ያለው አቅራቢ የሚጠየቀው የባለሙያዎች ብዛትና የዋስትና መጠን ሁሉንም ስርዓቶች የሚጠቀሙ ታክስ ከፋዮች ብዛትና አመታዊ ሽያጭ በአንድ ላይ በመደመር ይሆናል።

d) For a supplier having more than one licensed and operational sales register system, the required number of professionals and the amount of guarantee shall be determined based on the aggregate number of user taxpayers and annual sales volume across all of its systems.

ሠ/ በዚህ ንዑስ አንቀጽ 6 ፊደል ተራ (ለ) እና (ሐ) ላይ የተገለፀው እንደተጠበቀ ሆኖ አመታዊ ሽያጭ እና ተጠቃሚ ግብር ከፋይ ብዛት በማደግ ወይም በመቀነስ የምድብ ለውጥ መኖሩን በመከታተል የታክስ ባለስልጣኑ የዋስትና መጠኑን እና የባለሙያዎችን ብዛት በራሱ ሊወስን ይችላል።

e) Without prejudice to the provisions of sub-article 6 (b) and (c) herein, the Tax Authority may, by monitoring category changes resulting from increases or decreases in annual sales and the number of user taxpayers, determine the amount of the guarantee and the number of professionals on its own motion.

7/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 6(ሀ) የተገለፀውን የዋስትና መጠን እና የባለሙያዎችን ብዛት ባለስልጣኑ በበቂ ምክንያት ሊያሻሽለው ይችላል።

7/ The Authority may, for sufficient cause, revise the amount of the guarantee and the number of professionals specified under sub-article 6(a) of this Article.

15. የአቅራቢዎች ግዴታ

የኤሌክትሮኒክ የሽያጭ መመዝገቢያ ሶፍትዌር/ሥርዓት አቅራቢዎች የሚከተሉት ግዴታዎች ይኖርባቸዋል፤

15. Obligations of Suppliers

Suppliers of Electronic Sales Register Systems shall have the following obligations:

1/ ባለስልጣኑ በሥርዓቱ ላይ በማንኛውም ጊዜ ማሻሻያ በሚያደርግበት ወቅት በተቀመጠው የጊዜ ገደብ ውስጥ ማሻሻያውን የመተግበር፣

1/ To implement system updates within the specified timeframe whenever the Authority introduces modifications to the system at any time;

2/ በሥርዓቱ ላይ በባለስልጣኑ የሚሰጡ ማሻሻያዎች፣ የደህንነት ማስተካከያዎች እና መሰረታዊ ማሻሻያዎች በተቀመጠው የጊዜ ገደብ ውስጥ ለተጠቃሚ ታክስ ከፋዮች የማቅረብ፤

2/ To provide updates, security patches, and fundamental modifications issued by the Authority to user taxpayers within the specified timeframe;

3/ በማንኛውም ጊዜ ፈቃድ በተሰጠው ሥርዓት ላይ ለውጥ ከማድረጋቸው በፊት ለባለስልጣኑ የማሳወቅ፣

3/ To notify the Authority at any time before making modifications to the accredited system;

4/ ባለስልጣኑ ለሚያከናውነው የክትትልና ቁጥጥር ስራ ተባባሪ የመሆን እና የሚጠይቀውን መረጃና ሪፖርት በወቅቱ የማቅረብ፣

4/ To cooperate with the Authority in its monitoring and supervision activities and to provide the requested information and reports in a timely manner;

5/ በማንኛውም ጊዜ በታክስ ባለስልጣኑ ምርመራ በሚደረግበት ወቅት የደንበኞችን ዝርዝር እና የግብይት መረጃ ከሲስተም ሪፖርት በማውጣት የማቅረብ፣

5/ To extract and provide customer lists and transaction data from the system whenever an investigation is conducted by the Tax Authority;

6/ ታክስ ከፋዩ እና አቅራቢው በህግ ተቀባይነት ያለው ልዩ ስምምነት እስካልፈጸሙ ድረስ ማንኛውም ሶፍትዌር ለሶፍትዌሩ አሰራር ከሚያስፈልግ መረጃ ውጭ መረጃ መሰብሰብ፣ ከሶፍትዌሩ ውጭ ለሆነ ሌላ ሶፍትዌር ወይም መረጃ ቋት መረጃ ማስተላለፍ እንዲሁም የታክስ ከፋዩን መረጃ ለሌላ አገልግሎት ያለማዋል፣

6/ Unless a legally valid special agreement is concluded between the taxpayer and the supplier, any software shall not collect data other than what is required for its operation, transfer data to any other software or database outside of the system, or use the taxpayer's data for any other purpose;

7/ ለተጠቃሚ ታክስ ከፋዮች ደረጃውን የጠበቀ ጥገናና ድጋፍ የማድረግ እና ለሚሰጠው አገልግሎት የአገልግሎት ደረጃ ውል መስጠትና በዚሁ ስምምነት መሰረት አገልግሎት የማቅረብ፣

7/ To provide standardized maintenance and support to user taxpayers, and to issue and deliver services in accordance with this Service Level Agreement (SLA);

8/ ተጠቃሚ ታክስ ከፋዮች ስርዓቱን መጠቀም ሲጀምሩ እና ሲያቋርጡ ለታክስ ባለስልጣኑ የማሳወቅ፣

8/ To notify the Tax Authority whenever user taxpayers commence or terminate the use of the system;

16. **<u>የአቅራቢዎች ፈቃድ እድሳትና ስረዛ</u>**

16. **<u>Renewal and Cancellation of Supplier Licenses</u>**

1/ የኤሌክትሮኒክ የሽያጭ መመዝገቢያ ሥርዓት አቅራቢ ወይም አገልግሎት ሰጪ ፈቃድ በየሁለት አመቱ መታደስ አለበት።

2/ ለዕድሳት በሚቀርብበት ወቅት በዚህ መመሪያ አንቀጽ 15 የተቀመጡ ቅድመ ሁኔታዎች መሟላታቸውን በድጋሚ መረጋገጥ ይኖርበታል።

3/ አቅራቢው በዚህ መመሪያ የተጠቀሱትን ግዴታዎች በትክክል በማይወጣበት ወቅት እውቅናው ሊሰረዝ ወይም ሊታገድ ይችላል።

4/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 3 መሰረት ዕውቅናው ሲሰረዝ በአንቀጽ 17 በተጠቀሰው መሰረት ይፈጸማል።

1/ The license of an Electronic Sales Register System supplier or service provider shall be renewed every two years.

2/ Upon application for renewal, it must be re-verified that the pre-conditions set forth under Article 15 of this Directive are fully complied with.

3/ Where a supplier fails to properly fulfill the obligations specified under this Directive, its accreditation may be canceled or suspended.

4/ Where an accreditation is canceled pursuant to Sub-Article 3 of this Article, the execution shall be carried out in accordance with Article 17 of this Directive.

17. **<u>አገልግሎት ስለማቋረጥ</u>**

17. **<u>Termination of Service</u>**

1/ የኤሌክትሮኒክ የሽያጭ መመዝገቢያ ሥርዓት አቅራቢ ወይም አገልግሎት ሰጪ አገልግሎት በሚያቆምበት ጊዜ አገልግሎቱን ከማቆሙ ከስድስት ወራት በፊት አስቀድሞ ለባለስልጣኑና ለተጠቃሚ ታክስ ከፋዮች ማሳወቅ አለበት።

2/ የኤሌክትሮኒክ ደረሰኝ መመዝገቢያ ሥርዓት አቅራቢ ወይም አገልግሎት ሰጪ እውቅናው በአንቀጽ 16 መሰረት በሚሰረዝበት ጊዜ እውቅናው ከተሰረዘበት

1/ An Electronic Sales Register System supplier or service provider shall notify the Authority and user taxpayers six months in advance before terminating its services.

2/ Where an accreditation is canceled pursuant to Article 16, the supplier or service provider shall notify user taxpayers

ጊዜ ጀምሮ በአስር ቀናት ውስጥ ለተጠቃሚ ታክስ ከፋዮች ማሳወቅ አለበት።

3/ ባለስልጣኑ ተጠቃሚ ታክስ ከፋዮች ስራቸው ሳይስተጓጎል ወደ ሌላ አገልግሎት አቅራቢ የሚዘዋወሩበትን የመውጫ አማራጭ ስትራቴጂ ለባለስልጣኑ ማቅረብና ተቀባይነት ማግኘት አለበት።

4/ አቅራቢው አገልግሎቱን ባቋረጠ ወይም ፈቃዱ በተሰረዘ በስድስት ወራት ጊዜ ወስጥ ተጠቃሚ ታክስ ከፋዮች መረጃቸውን እንዲወስዱ ወይም ወደ ሌላ አገልግሎት ሰጪ እንዲያስተላልፉ ማድረግ አለበት።

5/ ሁሉም ተጠቃሚ ታክስ ከፋዮች ወደ ሌላ አገልግሎት ሰጪ መዛወራቸውን ወይም አማራጭ የሽያጭ መመዝገቢያ ስርዓት መጠቀማቸውን የሚያሳይ ሪፖርት ለአጽዳቂ ቡድን አቅርቦ ተቀባይነት ሲያገኝ ብቻ ስራ ስለማቆሙ ማረጋገጫ ይሰጠዋል፤ የዕውቅና ምስክር ወረቀቱንም ተመላሽ ያደርጋል።

within ten days from the date of such cancellation.

3/ The supplier shall submit to the Authority and obtain approval for an exit strategy that enables user taxpayers to transition to another service provider without disruption to their business operations.

4/ The supplier shall ensure that user taxpayers retrieve their data or transfer it to another service provider within six months from the date of termination of service or cancellation of the license.

5/ Confirmation of cessation of service shall be granted only upon the submission and approval of a report to the accreditation team, demonstrating that all user taxpayers have migrated to another provider or are using an alternative sales register system; the supplier shall also return the accreditation certificate.

18. የፍተሻ እና እውቅና አሰጣጥ አደረጃጀት

1/ ኤሌክትሮኒክስ ሽያጭ መመዝገቢያ ስርዓትን ለመፈተሽና እውቅና ለመስጠት የሚያስችል የቴክኒክ ቡድን እና እውቅና ሰጭ ቦርድ በሚኒስትር ወይም በሚኒስትር በሚወከል ኃላፊ ይቋቋማል፣

2/ የቡድኑ እና የቦርዱ የአንድ የስራ ዘመን ሁለት አመት ሲሆን እንደ አስፈላጊነቱ ለአንድ የስራ ዘመን ብቻ ሊራዘም ይችላል፣

18. Organization of Inspection and Accreditation

1/ A Technical Team and an Accreditation Board, responsible for testing and accrediting the Electronic Sales Register System, shall be established by the Minister or an official delegated by the Minister.

2/ One term of office for the Team and the Board shall be two years; it may be extended for only one

additional term as may be necessary.

3 የእውቅና ሰጭ ቦርድ አባላት በሚኒስትር ወይም በሚኒስትር በሚወከል ኃላፊ የሚመደብ ሆኖ በዋናነት፦

ሀ) በባለስልጣኑ የበላይ ኃላፊ የሚሰየም ....ሰብሳቢ

ለ) ኤሌክትሮኒክስ ሽያጭ መመዝገቢያ የሚያስተዳድር የስራ ክፍል ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር…አባልና ጸሃፊ

ሐ) የቴክኒክ ቡድን ሰብሳቢ...............አባል

መ) የታክስ ኢንተለጀንስ ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር ....አባል

ሠ) የታክስ ማስታወቅ ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር .... አባል

ረ) የሶፍትዌር ልማት ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር ....አባል

ሰ) የታክስ ሥርዓት ማጣጣምና የክልሎች ድጋፍ ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር ....አባል

ሸ) ሁለት ከክልልና ከተማ አስተዳደር የሚወከሉ አባላት፣

4 የቴክኒክ ቡድን አባላት ምደባና ብዛት፣

የሚከተሉት የቴክኒክ ቡድን አባላት በሚኒስትር ወይም ሚኒስትር በሚወክለው ኃላፊ ይመደባሉ፤

3/ The members of the Accreditation Board shall be assigned by the Minister or an official delegated by the Minister and shall consist of:

a) An official designated by the Head of the Authority .... Chairperson

b) The Director of the Directorate responsible for administering the Electronic Sales Register System...............Member and Secretary

c) The Chairperson of the Technical Committee .... Member

d) The Director of the Tax Intelligence Directorate .... Member

e) The Director of the Tax Filing Directorate ...... Member

f) Software Development Directorate Director…Member

g) Tax harmonization and Regional Support Directorate director........ Member

h) Two representatives from Regional and City Administration Revenue Authorities ...... Member.

4/ Assignment and Number of Technical Team Members;

The following members of the Technical Team shall be assigned

by the Minister or an official delegated by the Minister:

ሀ) ከሶፍትዌር ልማት ዳይሬክቶሬት የሚመደብ የቡድን መሪ ወይም ከፍተኛ ባለሙያ ....ሰብሳቢ

ለ) ከኤሌክትሮኒክስ ሽያጭ መመዝገቢያ የስራ ክፍል የሚመደብ ባለሙያ/ቡድን............ አባልና ጸሃፊ

ሐ) ከፍተኛ የኤሌክትሮኒክስ ሽያጭ መመዝገቢያ ባለሙያ..................አባል

መ) ሦስት ከፍተኛ የሶፍትዌር ልማት ባለሙያዎች ....አባላት

ሠ) ሶስት ተጨማሪ አባላት እንደ አስፈላጊነቱ ሊመደቡ ይችላል

ረ) የቡድኑ አባላት ሰብሳቢን ጨምሮ ከዘጠኝ ሊበልጥ አይችልም።

5 የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 4 ቢኖርም ሌላ ተቋም የቴክኒክ ፍተሻ ሥራውን እንዲያከናውን ባለስልጣኑ ውክልና ሊሰጥ ይችላል፣

6 የእውቅና ሰጭ ቦርድ ተግባርና ኃላፊነት

ሀ) በቀረቡ ሰነዶች መሠረት የግብር ከፋዩን ህጋዊነት ያጣራል፣

ለ) በአቅራቢው ወይም በግብር ከፋዩ የሚያቀርበውን የባንክ ወይም የኢንሹራንስ ዋስትና ሰነድ ህጋዊነትና በዚህ መመሪያ መሰረት መሆኑን ያረጋግጣል፣

a) A representative from Software Development Directorate Team Lead or Senior Engineer .... Chairperson

b) Arepresentative rofessional or team leader from the Department responsible for administering the Electronic Sales Register System……. Member and Secretary

c) Senior Electronic Sales Register System Expert ….……Member

d) Three Senior Software Engineers …………………… Members

e) Three additional members may be assigned as necessary.

f) The number of members of the Team, including the Chairperson, shall not exceed nine.

5/ Notwithstanding sub-article (4) of this Article, the Authority may delegate another institution to perform the technical inspection task.

6/ Powers and Duties of the Accreditation Board

a) It shall verify the legality of the taxpayer based on the submitted documents;

b) It shall verify the legality of the bank or insurance guarantee document submitted by the supplier or the taxpayer and ensure its

compliance with this Directive;

ሐ) በዚህ መመሪያ አንቀፅ 14 ንዑስ አንቀጽ 6 መሰረት አቅራቢዎች የዋስትና እና ባለሙያ ማሟላታቸውን ያረጋግጣል፣

c) It shall ensure the compliance of suppliers with the guarantee and professional staffing requirements in accordance with Article 14, sub-article 6 of this Directive;

መ) የአቅራቢን እና የሽያጭ መመዝገቢያ ሥርዓትን እድሳትና ፈቃድ ስረዛ ያጸድቃል፣

d) It shall provide for approval for the renewal and license revocation of the supplier and the sales register system;

ሠ) ለእውቅና የቀረበ ሽያጭ መመዝገቢያ ሥርዓት በዚህ መመሪያ መሰረት በቴክኒክ ቡድኑ መፈተሹን ያረጋግጣል፣ የተጠየቁ የሰነድ ማስረጃዎችን ትክክለኛነትና ተገቢነት ይመረምራል፣ ያጸድቃል፣

e) It shall ensure that the sales register system submitted for accreditation has been tested by the Technical Team in accordance with this Directive; it shall examine and provide for approval to the authenticity and appropriateness of the required documentary evidence.

ረ) የቴክኒክ ቡድን የሚያስፈልገውን እገዛ ያደርጋል፣

f) It shall provide the necessary support to the Technical Team.

ሰ) ቴክኒክ ቡድኑ የሚያዘጋጀውን የሥርዓት መፈተሽ ቅፅ፣ አሰራር ሥርዓት እና መርሃ ግብር ይገመግማል፣ ያጸድቃል፣

g) It shall review and provide for approval the system testing form, procedures, and schedule prepared by the Technical Team.

ሸ) የቴክኒክ ቡድኑን የፍተሻ ውጤት ይገመግማል፣ ያጸድቃል፣

f) It shall review and approve the testing results of the Technical Team.

ቀ) በዚህ መመሪያ አንቀጽ 14 መሰረት ለአቅራቢነት የሚቀርብ ግብር ከፋይ የሚጠበቅበትን ሲያሟላ የአቅራቢነት ፈቃድ እንዲሰጠው የውሳኔ ሃሳብ ለኢ-ዳታ ዘርፍ ሚኒስትር ዴኤታ ያቀርባል።

i) When a taxpayer applying for supplier status fulfills the requirements set forth under Article 14 of this Directive, the Board shall submit a recommendation to the State Minister of the

E-Data Division for the issuance of the supplier license.

በ) በዚህ መመሪያ አንቀጽ 5፣6 እና 7 መሰረት ለእውቅና የሚቀርብ የሽያጭ መመዝገቢያ ሥርዓት የሚጠበቅበትን ሲያሟላ እውቅና እንዲሰጠው የውሳኔ ሃሳብ ለኢ-ዳታ ዘርፍ ሚኒስትር ዴኤታ ያቀርባል

j) When a sales register system submitted for accreditation fulfills the requirements set forth under Articles 5, 6, and 7 of this Directive, the Board shall submit a recommendation to the State Minister of the E-Data Division for its accreditation.

ተ) በኤሌክትሮኒክ ደረሰኝ መመዝገቢያ ሥርዓት ላይ የሚደረግን እና በታክስ ከፋዮች ሥርዓት ላይ ለውጥ ማድረግን የሚጠይቅን ለውጥ ይገመግማል፣ ያፅድቃል፣ በአቅራቢዎች እና በታክስ ከፋዮች የሚተገበርበትን መርሃ ግብር ያወጣል፣

k) It shall review and approve changes made to the electronic invoice registration system that require modifications to taxpayers' systems; it shall also issue the implementation schedule to be followed by suppliers and taxpayers.

ቸ) በሽያጭ መመዝገቢያ ሥርዓቶች የማሻሻል ጥያቄ በሚቀርብበት ወቅት በቴክኒክ ቡድን የሚቀርበውን የማሻሻያውን ደረጃ ግምገማ ውጤት ይመረምራል፣ ያጸድቃል፣

l) When a request for modification to a sales register system is submitted, the Board shall examine and approve the assessment results provided by the Technical Team regarding the level of the modification.

7 የቴክኒክ ቡድኑ ተግባርና ኃላፊነት

7/ Powers and Duties of the Technical Team

ሀ) በአንቀጽ 9 እና 10 በተመለከተው መሰረት የቀረበው የሽያጭ መመዝገቢያ ሥርዓት ተስማሚነቱን በፍተሻ ያረጋግጣል፤

a) It shall verify the suitability of the submitted sales register system through testing, in accordance with Articles 9 and 10.

ለ) የሽያጭ መመዝገቢያ ስርዓቱ የፍተሻ መስፍረቱን ማሟላቱን የቴክኒክ ቡድን አባላት በሁለት ሶስተኛ ድምጽ በፊርማቸው ማጽደቅ ይኖርባቸዋል፤

b) Members of the Technical Team must approve the fulfillment of the sales register system's testing

criteria by a two-thirds majority vote and their signatures.

ሐ) አቅራቢዎች በአንቀጽ 14 የተጠቀሰውን መስፈርት ስለማሟላታቸው በቴክኒክ ቡድን ይጣራል፣ ይፈተሻል፤

c) The Technical Team shall investigate and verify whether the suppliers fulfill the requirements specified under Article 14,

መ) በዚህ መመሪያ አንቀጽ 5፣6 እና 7 መሰረት እውቅና የሚቀርብ የሽያጭ መመዝገቢያ ሥርዓት የሚጠበቅበትን እንደሚያሟላ ለማረጋገጥ የሚያስፈልገውን የፍተሻ ሂደት፣ የፍተሻ መጠይቅ እና አሰራር ስርዓት ይቀርጻል፣ በእውቅና ሰጭ ቦርድ ሲፀድቅ ተግባራዊ ያደርጋል፤

d) It shall design the testing process, testing questionnaire, and operating procedures required to ensure that a sales register system submitted for accreditation fulfills the requirements under Articles 5, 6, and 7 of this Directive; it shall implement the same upon approval by the Accreditation Board.

ሠ) በዚህ መመሪያ አንቀጽ 5፣6 እና 7 መሰረት ለእውቅና የሚቀርብ የሽያጭ መመዝገቢያ ሥርዓት የሚጠበቅበትን ሲያሟላ እውቅና እንዲሰጠው የፍተሻ ውጤት ለእውቅና ሰጭ ቦርድ ያቀርባል፤

e) The Technical Team shall submit the testing results to the Accreditation Board for the accreditation of a sales register system that fulfills the requirements set forth under Articles 5, 6, and 7 of this Directive.

ረ) ለእውቅና በሚቀርቡ ሥርዓቶችና አቅራቢዎች የሚቀርቡ ማስረጃዎችን ይመረምራል፣ ያጣራል፤

f) The Technical Team shall examine and investigate the evidence submitted by the systems and suppliers applying for accreditation.

ሰ) የሽያጭ መመዝገቢያ ሥርዓት አገልግሎት አቅራቢዎች የተቀመጠውን መሰረተ-ልማት ማሟላታቸውን ለማረጋገጥ እንደ አስፈላጊነቱ የአቅራቢውን መረጃ ማዕከል በአካል ይመለከታል፣ ይገመግማል፣ የግምገማ ሪፓርት ለእውቅና ሰጭ ቦርድ ያቀርባል፤

g) To ensure that sales register system service providers fulfill the established infrastructure (data center) requirements, the Technical Team shall, as necessary, physically inspect and evaluate the provider's data center and submit an

evaluation report to the Accreditation Board.

ሸ) የአቅራቢዎች እና የሽያጭ መመዝገቢያ ሥርዓቶች ለእድሳት በሚቀርቡበት ጊዜ በዚህ መመሪያ መሰረት የእድሳት ፍተሻ ያደርጋል፤

h) Upon the submission of renewal applications for suppliers and sales register systems, the Technical Team shall conduct a renewal inspection in accordance with this Directive.

ቀ) በሽያጭ መመዝገቢያ ሥርዓት ላይ የማሻሻል ጥያቄ በሚቀርብበት ወቅት የማሻሻያውን ደረጃ ይገመግማል፣ ውጤቱን ለእውቅና ሰጭ ቦርድ ያቀርባል፣ እንደ አስፈላጊነቱ የማሻሻያ ፍተሻ ያደርጋል፤

i) When a request for modification to a sales register system is submitted, the Technical Team shall assess the level of the modification and submit the results to the Accreditation Board; it shall also conduct a modification test as necessary.

8 የኢ-ዳታ ዘርፍ ተግባርና ኃላፊነት

8/ Powers and Duties of the e-Data Division

ሀ) የእውቅና ሰጭ ቦርድ እና የቴክኒክ ቡድን በበላይነት ይመራል፤

a It shall provide overall leadership and oversight to the Accreditation Board and the Technical Team.

ለ) የእውቅና ሰጭ ቦርድ ቃል ጉባኤ እና የፍተሻ ውጤት መርምሮ ውሣኔ ይሰጣል፤

b The State Minister of the E-Data Division shall examine the minutes of the Accreditation Board and the testing results and render a final decision.

ሐ) ለቴክኒክ ቡድን እና የእውቅና ሰጭ ቦርድ የሚያስፈልጋቸውን እገዛ ያደርጋል፤

c) It shall provide the necessary support to the Technical Team and the Accreditation Board.

መ) በእውቅና ሰጭ ቦርድ ጸድቆ የሚመጣውን የሽያጭ መመዝገቢያ ሥርዓት እና አቅራቢ እውቅና ይሰጣል፤

d It shall grant accreditation to the sales register system and the supplier upon the approval of the Accreditation Board.

ሠ) የሽያጭ መመዝገቢያ ሥርዓት ወይም አቅራቢ በቴክኒክ ቡድን እና በእውቅና ሰጭ ቦርድ ተገምግሞ ተቀባይነት ሲያገኝ በቦርዱ ሰብሳቢ እና በኢ-ዳታ ዘርፍ ሚኒስትር ዴኤታ በጋራ የተፈረመ የእውቅና የምስክር ወረቀት ይሰጣል፤

e) When a sales register system or a supplier is evaluated and accepted by the Technical Team and the Accreditation Board, a Certificate of Accreditation jointly signed by the Chairperson of the Board and the State Minister of the E-Data Division shall be issued.

ክፍል አራት

የኤሌክትሮኒክ ደረሰኝ አጠቃቀም

SECTION FOUR

Utilization of Electronic Invoicing

19. የኤሌክትሮኒክ ሽያጭ መመዝገቢያ ሥርዓት ስለመጠቀም

1/ ከኤሌክትሮኒክ ደረሰኝ መመዝገቢያ ሥርዓት ጋር ተስማሚ የሆነ የኤሌክትሮኒክ ሽያጭ መመዝገቢያ ሥርዓት መጠቀም በሁሉም በታክስ ሕጉ መሰረት የሂሳብ መዝገብ በሚይዙ ታክስ ከፋዮች ላይ ተፈጻሚ ነው።

2/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ላይ የተደነገገው ቢኖርም ማንኛውም ታክስ ከፋይ በፈቃደኝነት ከኤሌክትሮኒክ ደረሰኝ መመዝገቢያ ሥርዓት ጋር ተስማሚ የሆነ የኤሌክትሮኒክ ሽያጭ መመዝገቢያ ሥርዓት መጠቀም ይችላል።

3/ በአባሪ ሁለት በተዘረዘሩት ዘርፎች የተሰማሩ ታክስ ከፋዮች የሚጠቀሙት የሽያጭ መመዝገቢያ ስርዓት ግዴታ ከቀጥታ ግንኙነት ውጭ የሚሰራ መሆን ይኖርበታል።

4/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 3 ላይ የተደነገገው ቢኖርም የታክስ ባለስልጣኑ ከቀጥታ ግንኙነት ውጭ የሚሰራ የሽያጭ መመዝገቢያ ስርዓት የመጠቀም ግዴታ የሚሆንባቸውን ዘርፎች ማሻሻል ይችላል።

19. Utilization of Electronic Sales Register System

1/ The use of an Electronic Sales Register System that is integrated with the Electronic Invoice Registration System is mandatory for all taxpayers that maintain books of accounts as per the tax law.

2/ Notwithstanding the provisions of sub-article 1 of this Article, any taxpayer may voluntarily use an electronic sales register system that is compatible with the Electronic Invoice Registration System.

3/ The sales register system utilized by taxpayers engaged in the sectors listed under Annex Two must mandatorily function in an offline mode.

4/ Notwithstanding the provisions of sub-article 3 of this Article, the Tax Authority may modify the sectors for which the use of an offline sales register system is mandatory.

5/ ግብር ከፋይ ፈቃድ የተሰጠውን የኤሌክትሮኒክ የሽያጭ መመዝገቢያ ሥርዓት/ሶፍትዌር ወይም የኤሌክትሮኒክ የሽያጭ መመዝገቢያ ሥርዓት አገልግሎት ወይም ታክስ ከፋዩ ለራሱ ብቻ የሚጠቀምበት የኤሌክትሮኒክስ የሽያጭ መመዝገቢያ ሥርዓት ለመጠቀም፦

ሀ) በባለስልጣኑ የታክስ ከፋይ የድረ-ገጽ አገልግሎት ማዕከል ለኤሌክትሮኒክ ደረሰኝ ተጠቃሚነት በመመዝገብ የስርዓት መለያ ቁጥር ፣ የግንኙነት ቁልፍ እና የተጠቃሚ የሚስጥር ቁልፍ መውሰድ ይኖርበታል፣

ለ) በታክስ ከፋዩ ስም/የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር እና በተመዘገበው ሶፍትዌር/ስርዓት መለያ ቁጥር በመጠቀም የዲጂታል ፊርማ ሰርተፍኬት ከኢንፎርሜሽን መረብ ደህንነት አስተዳደር ወይም ፈቃድ ካለው አካል መውሰድ ይኖርበታል፣

ሐ) በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 2 "ሀ" እና "ለ" የተገኘውን መረጃ በመጠቀም የኤሌክትሮኒክ የሽያጭ መመዝገቢያ ሥርዓት/ሶፍትዌር ለስራ ዝግጁ በማድረግ መጠቀም ይችላሉ።

6/ ታክስ ከፋይ በተሰጠው የደረሰኝ ሶፍትዌር ፈቃድ በኢኮሜርስ ወይም ዲጂታል ገበያ ቦታ ለመጠቀም፦

ሀ) በባለስልጣኑ የታክስ ከፋይ የድረ-ገጽ አገልግሎት ማዕከል ለኤሌክትሮኒክ ደረሰኝ ተጠቃሚነት መመዝገብና የሚጠቀመውን ኢኮሜርስ ወይም ዲጂታል ገበያ ቦታ በማመላከት የተጠቃሚ የሚስጥር ቁልፍ ቃል መውሰድ ይኖርበታል፣

5/ To utilize an authorized electronic sales register system/software, an electronic sales register system service, or an electronic sales register system developed by the taxpayer for their own exclusive use:

a) The taxpayer shall register for the electronic invoicing service through the Authority's Taxpayer Portal and obtain a System Number, an API Key, and a Client Secret.

b) The taxpayer must obtain a Digital Signature Certificate from the Information Network Security Administration (INSA) or an authorized body, by using the taxpayer's Name/Tax identification number and the registered system number.

c) Taxpayers may utilize the electronic sales register system/software by configuring it using the information obtained under sub-article 2 (a) and (b) of this Article.

6/ Tax payer to utilize invoice software on an authorized e-commerce platform or digital market place:

a) The taxpayer shall register for electronic invoicing through the Authority's Taxpayer Portal and obtain a Client Secret by specifying the e-commerce platform or

digital marketplace they utilize.

ለ) በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ ሀ የተገኘውን መረጃ በመጠቀም ኢኮሜርስ ወይም ዲጂታል ገበያ ቦታ ሥርዓት/ሶፍትዌር ለስራ ዝግጁ በማድረግ መጠቀም ይችላሉ።

b) Taxpayers may utilize the e-commerce or digital marketplace system/software by configuring it using the information obtained under sub-article (a) of this Article.

20. የኤሌክትሮኒክ ሽያጭ መመዝገቢያ ስርዓት መጠቀም የማይገደዱ

20. Exemptions from the Obligation to Use Electronic Sales Register System

1/ በዚህ መመሪያ አንቀጽ 19 ንዑስ አንቀፅ 1 የተጠቀሰው ቢኖርም በርካታ ደረሰኞችን የሚያመነጩና አሰራራቸው ለኦዲት እና ክትትል አመቺ የሆኑ ባንኮች፣ የሰነደ-መዋለ ነዋይ ገበያዎች፣ የዲጂታል ክፍያ አሳላጮች፣ የቴሌኮም አገልግሎት በማቅረብ የተሰማሩ ታክስ ከፋዮች፣ ለሸማች ወይም የግል አገልግሎት በሚውሉ ግብይቶችና አገልግሎቶች ላይ ከኤሌክትሮኒክ ደረሰኝ መመዝገቢያ ስርዓት ጋር በቀጥታ መገናኘት ሳያስፈልጋቸው ደረሰኝ የሚሰጡበትን አሰራር ባለስልጣኑ በልዩ ሁኔታ ሊፈቅድ ይችላል።

1/ Notwithstanding the provisions of Article 19(1) of this Directive, the Authority may, under special circumstances, authorize taxpayers engaged in banking, securities markets, digital payment processing, and telecommunications services whose operations generate high volumes of invoices and are conducive to audit and monitoring to issue invoices for consumer transactions and services without the need for a direct connection to the Electronic Invoicing System.

2/ በዚህ አንቀጽ በንዑስ አንቀጽ 1 ከተዘረዘሩት በተጨማሪ ሌሎች ዘርፎች ተመሳሳይ አሰራር እንዲከተሉ ሚኒስቴሩ ሊወስን ይችላል።

2/ In addition to those listed under sub-article (1) of this Article, the Ministry may permit other sectors to follow a similar approach.

3/ በዚህ አንቀጽ መሰረት ፈቃድ የሚሰጠው፣

ሀ) የሚሰጠው ደረሰኝ ቢያንስ በተጨማሪ እሴት ታክስ ደንብ ቁጥር 570/2017 አንቀጽ 20 የተዘረዘረውን የደረሰኝ ይዘት የያዘ እና ከዚህ መመሪያ ጋር በተያያዘው የደረሰኝ ናሙና አባሪ 1 ላይ የተመለከቱትን ዝርዝር መረጃዎች መያዝ አለበት፣

3/ Authorization granted under this Article shall be;

a) The invoice to be issued shall, at a minimum, contain the particulars of an invoice as specified under Article 20 of the Value Added Tax Regulation No. 570/2026 and shall include the

detailed information indicated in annex 1 in the sample receipt attached to this Directive.

ለ) የሽያጩን የተጠቃለለ መረጃ በሚሰጠው የጊዜ ገደብ ውስጥ ለግብር ባለስልጣኑ ማሳወቅ አለበት፣

b) The taxpayer shall report the summary of sales information to the Tax Authority within the prescribed time limit.

ሐ) የተጠቃለለው የሽያጭ መረጃ የሽያጭ ጊዜ ከ እስከ ከ፣ የተሰጠ አገልግሎት ወይም እቃ አይነት፣ ብዛት፣ የነጠላ ዋጋ፣ ጠቅላላ ዋጋ፣ የተጣለ ታክስ አይነት፣ የታክስ መጣኔ፣ የታክስ መጠን እና ጠቅላላ ድምር መያዝ አለበት፣

c) The summarized sales information shall include the sales period (from/to), the type of service rendered or goods sold, quantity, unit price, total price, type of tax imposed, tax rate, tax amount, and the grand total.

መ) የተጠቃለለው የሽያጭ መረጃ የማስተላለፊያ ጊዜ እንደ ታክስ ከፋዩ የንግድ ዘርፍ በባለስልጣኑ የሚወሰን ሆኖ በቀን፣ በሳምንት ወይም በወር ሊሆን ይችላል፣

d) The transmission period for the summarized sales information shall be determined by the Authority based on the taxpayer's business sector and may be on a daily, weekly, or monthly basis.

ሠ) እያንዳንዱን ደረሰኝ መረጃ በህግ ለተደነገገው ጊዜ ማስቀመጥና በተጠየቀ ጊዜ ለባለስልጣኑ በዲጂታል አማራጭ ወይም ታትሞ መስጠት ይኖርበታል፣

e) Each invoice data shall be stored for the period prescribed by law and, upon request, shall be provided to the Authority either in a digital format or in a printed hard copy.

ረ) ለእያንዳንዱ ደረሰኝ ልዩ የደረሰኝ ቁጥር እና ፈጣን መላሽ ኮድ ሊኖረው ይገባል፣

f) Each invoice shall have a unique invoice number and a Quick Response (QR) code.

ሰ) ታክስ ከፋዩ የደረሰኙን ትክክለኛነት ለማረጋገጥ የሚያገለግል ለህዝብ ክፍት የሆነ የደረሰኝ ማረጋገጫ አገልግሎት ሊኖረው ይገባል፣

g) The taxpayer shall provide a publicly accessible invoice verification service to validate the authenticity of the invoice.

4/ በዚህ አንቀጽ መሰረት ፈቃድ ለሚጠይቁ ታክስ ከፋዮች ለሲስተሙና ለስራ ዘርፉ ተስማሚ የሆነ የፍተሻ መስፈርትና ቅድመ ሁኔታ እንዲሁም ልዩ ስምምነት ውል ባለስልጣኑ ያዘጋጃል፣

4/ The Authority shall prepare inspection criteria, prerequisites, and a special contractual agreement suitable for the system and the business sector for taxpayers requesting authorization under this Article.

5/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 የተፈቀደው እንደተጠበቀ ሆኖ ግብይቱ ከሌላ ከተመዘገበ ታክስ ከፋይ ጋር በሚሆንበት ጊዜ እና ደረሰኙ ለግብር ማሳወቅ የሚውል ሲሆን ከኤሌክትሮኒክ ደረሰኝ መመዝገቢያ ሥርዓት ጋር በቀጥታ በመገናኘት እና በአንቀጽ 3 መሰረት ደረሰኙ መመዝገብ ይኖርበታል፣

5/ Notwithstanding the provisions of sub-article (1) of this Article, where a transaction is between registered taxpayers (B2B) and the invoice is intended for tax reporting purposes, it must be registered in accordance with Article 3 through a direct connection with the Electronic Invoice Registration System.

6/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 4 በተጠቀሰው መሰረት የተመዘገበ ደረሰኝ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 መሰረት በሚላከው የተጠቃለለ ሪፓርት ውስጥ አይካተትም።

6/ An invoice registered in accordance with sub-article (4) of this Article shall not be included in the summarized report transmitted pursuant to sub-article (2) of this Article.

21. የባለስልጣኑን የክላውድ የሽያጭ መመዝገቢያ ሥርዓት/ሶፍትዌር ስለመጠቀም

21. Regarding the Utilization of the Authority's Cloud Sales Register System

የባለስልጣኑን የክላውድ የሽያጭ መመዝገቢያ ሥርዓት መጠቀም የሚቻለው፤

1/ አዲስ ወደ ስራ የሚገባ ታክስ ከፋይ ፈቃድ የተሰጠውን የሽያጭ መመዝገቢያ ሥርዓት ስራ ላይ እስኪያውል ድረስ ታክስ ከፋዩ ፈቃድ ከወሰደ ጀምሮ በሚቆጠር ከሁለት ወር ላልበለጠ ጊዜ፣

2/ ታክስ ከፋዩ ፈቃድ ካላቸው የሽያጭ መመዝገቢያ ሥርዓት ወይም ከአገልግሎት ሰጪዎች ለመጠቀም የሚያስችል አቅም የሌለው መሆኑን ባለስልጣኑ በተገቢው ማስረጃ ሲያረጋግጥና ፈቃድ ሲሰጥ፤

The Authority's Cloud Sales Register System may be utilized where:

1/ For a newly registered taxpayer, for a period not exceeding two months from the date of obtaining a business license, until such taxpayer implements an authorized sales register system,

2/ Where the Authority, upon verification of appropriate evidence, confirms that the taxpayer lacks the capacity to utilize an authorized sales register system or services from

providers, and grants authorization [to use the Cloud System];

3/ የታክስ ከፋዩ የግብይት ሁኔታ ወይም በተሰማራበት የንግድ ዘርፍ አይነት ላይ በመመስረት የታክስ ባለሥልጣኑ ታክስ ከፋዩ የክላውድ ደረሰኝ ሥርዓት እንዲጠቀም ያስገደደው ወይም የፈቀደለት ከሆነ፤

3/ Where the Tax Authority, based on the nature of the taxpayer's transactions or the type of business sector, requires or authorizes the taxpayer to utilize the Cloud Invoicing System,

4/ የታክስ ከፋዩ የሽያጭ መመዝገቢያ ሥርዓት ጉድለት ከተገኘበት ወይም አስገዳጅ ማስተካከያዎች እንዲያደርግ ተጠይቆ ይህ ማስተካካያ እስኪደረግ ወይም ግብር ከፋዩ ሌላ የሽያጭ መመዝገቢያ ሥርዓት እስኪጠቀም፣

4/ Where a defect is found in the taxpayer's sales register system, or where mandatory adjustments have been requested, until such adjustments are implemented or until the taxpayer utilizes another sales register system,

5/ ታክስ ከፋዩ የሚጠቀምበት የሽያጭ መመዝገቢያ ሥርዓት ወይም አቅራቢው ሲታገድ ወይም አገልግሎት ሲያቆም ባለስልጣኑ ሲፈቅድና ታክስ ከፋዩ ሌላ የሽያጭ መመዝገቢያ ሥርዓት መጠቀም እስኪችል ድረስ፣

5/ Where the sales register system used by the taxpayer or its provider is suspended or ceases operation, upon the Authority's authorization and until the taxpayer is able to utilize another sales register system,

6/ የታክስ ከፋዩ የሽያጭ መመዝገቢያ ሥርዓት በልዩ ልዩ ምክንያት በአጭር ጊዜ ለማስተካከል የማይቻል ችግር ሲያጋጥመውና ታክስ ከፋዩ መጠቀም የማይችልበት ሁኔታ ሲኖር ይህንኑ ለባለስልጣኑ በማሳወቅና ችግሩ ተቀርፎ ወደስራ እስኪመለስ ድረስ፣

6/ Where the taxpayer's sales register system encounters a defect that cannot be rectified within a short period due to various reasons, and the taxpayer is unable to utilize it, upon notifying the Authority and until such problem is resolved and operations resume

22. ባለ ፈጣን መላሽ ማንዋል ደረሰኝ ስለመጠቀም

22. Regarding the Use of Manual Invoices with Quick Response (QR) Codes

1/ ታክስ ከፋይ ባለ ፈጣን መላሽ ማንዋል ደረሰኝ መጠቀም የሚችለው

ሀ) የኤሌክትሮኒክ ደረሰኝ መመዝገቢያ ሥርዓት አገልግሎት በማይሰጥበት ጊዜ፣

1/ A taxpayer may utilize manual invoices with Quick Response (QR) codes where:

a) Procedures to be followed when the Electronic Invoice

Registration System is non-functional.

(1) በባለስልጣኑ በታወቀ ምክንያት ወይም በአስገዳጅ ሁኔታ የኤሌክትሮኒክ ደረሰኝ መመዝገቢያ ሥርዓት አገልግሎት የማይሰጥ መሆኑን ለታክስ ከፋዮች በተለያዩ የህዝብ መገናኛ ዘዴዎች ሲያሳውቅ፣

(1) Where the Authority, due to a known reason or force majeure, notifies taxpayers through various public media outlets that the Electronic Invoicing System is non-functional;

(2) ከቀጥታ ግንኙነት ውጭ የሚሰራ የሽያጭ መመዝገቢያ ሶፍትዌር ከሆነ የተመዘገበው የመጠባበቂያ ደረሰኝ ሙሉ በሙሉ ስራ ላይ ውሎ ተጨማሪ ማግኘት ካልቻለ፣

(2) Where the sales register software operates offline, and the registered backup (Temporary) invoices are fully utilized such that no additional invoices can be obtained;

(3) የታክስ ከፋዩ የንግድ ሁኔታ ግንኙነት በተቋረጠበት ወቅት ደረሰኙን ካልቆረጠ ግብይቱን የሚያሳጠው ከሆነ፣

(3) Where the nature of the taxpayer's business is such that failure to issue an invoice during a system interruption would result in a loss of the transaction;

ለ) የታክስ ከፋዩ የሽያጭ መመዝገቢያ ሥርዓት በማይሰራበት ጊዜ

b) A procedure when the taxpayer’s sales register system is non-functional:

(1) ፈቃድ ካለው አቅራቢ የተገኘ ሽያጭ መመዝገቢያ ስርዓት ከሆነ ችግሩን ለአቅራቢው በማሳወቅ አቅራቢው ችግሩ በሁለት ሰዓት ውስጥ እንደማይፈታ ማረጋገጫ ሲሰጥ፣

(1) Where the sales register system is obtained from an authorized provider, upon notifying the provider of the defect and receiving confirmation from the provider that the problem cannot be resolved within two hours;

(2) የባለስልጣኑ የክላውድ ሽያጭ መመዝገቢያ ሥርዓት ስራውን

(2) Where the taxpayer is unable to resume

ለማስቀጠል የማያስችለው ሲሆን፣

(3) የችግሩን ምንጭ፣ አይነት፣ መጠን፣ በማን እንደሚጠገን እና ጥገናው የሚጠይቀውን ጊዜ ለታክስ ባለስልጣኑ በማሳወቅ፣

ሐ) በባለስልጣኑ የታወቀ በርካታ ታክስ ከፋዩችን የሚመለከት የመረጃ ቴክኖሎጂ መሰረተ ልማት ወይም የሃይል መቋረጥ ሲኖርና ባለስልጣኑ በተናጠል ወይም በተለያዩ የህዝብ መገናኛ ዘዴዎች ፈቃድ ሲሰጥ፣

መ) የታክስ ባለስልጣኑን የክላውድ ሽያጭ መመዝገቢያ ሥርዓት ለሚጠቀም ታክስ ከፋይ ሥርዓቱ በማይሰራበት ጊዜና ይህንኑ ለባለስልጣኑ ሲያሳውቅ፣

ሠ) ታክስ ከፋዩ የስራ ዘርፍና ሁኔታ የሚስማማ ሽያጭ መመዝገቢያ ሥርዓት አለመኖሩ ከታመነበትና ባለስልጣኑ ለታክስ ከፋዩ ወይም ለዘርፉ በልዩ ሁኔታ ሲፈቅድ፣

2/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 በተጠቀሱት ምክንያቶች ባለ ፈጣን መላሽ የወረቀት/ማንዋል ደረሰኝ መጠቀም የሚቻለው ችግሩ እስከሚፈታ ብቻ ነው፣

operations via the Authority's Cloud Sales Register System

(3) By notifying the Tax Authority of the cause, type, and extent of the problem, the person responsible for the repair, and the estimated time required for completion

c) Where there is a known large-scale Information Technology infrastructure (Network) or power interruption affecting numerous taxpayers, and the Authority grants authorization individually or through various public media outlets

d) For a taxpayer utilizing the Authority's Cloud Sales Register System, where the system is non-functional and the taxpayer notifies the Authority of such failure;

e) Where it is determined that there is no sales register system compatible with the taxpayer's line of business or operational conditions, and the Authority grants a special authorization to the taxpayer or the specific sector;

2/ The use of manual paper invoices with Quick Response (QR) codes for the reasons specified under sub-article (1) of this Article shall be permitted only until the problem is resolved.

3/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ፊደል ተራ (ለ) መሰረት ችግሩን ለመፍታት ከሰባት ቀን በላይ የሚወስድ ከሆነ ታክስ ከፋዩ በጊዜያዊነት ወይም በቋሚነት ሌላ ሽያጭ መመዝገቢያ ሥርዓት መጠቀም ይኖርበታል፣

4/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 3 ቢኖርም እንደ ታክስ ከፋዩ ሁኔታና የችግሩ ስፋት ባለ ፈጣን መላሽ የወረቀት/ማንዋል ደረሰኝ የመጠቀም ጊዜ ባለስልጣኑ በልዩ ሁኔታ ሊያሻሽል ይችላል፤

5/ በዚህ አንቀፅ በተፈቀደው መሰረት ባለ ፈጣን መላሽ የወረቀት/ማንዋል ደረሰኝ የተጠቀመ ታክስ ከፋይ፦

ሀ) ያጋጠመው ችግር በተፈታ እና ከኤሌክትሮኒክ ደረሰኝ መመዝገቢያ ሥርዓት ጋር ያለው ግንኙነት በቀጠለ በ72 ሰዓት ውስጥ በባለ ፈጣን መላሽ የወረቀት ደረሰኝ የተከናወኑ ግብይቶችን በሙሉ የደረሰኝ ቁጥርን በማጣቀስ በታክስ ባለስልጣኑ የኤሌክትሮኒክ ደረሰኝ መመዝገቢያ ሥርዓት መመዝገብ አለበት።

ለ) የገዢው የታክስ ከፋይ መለያ ቁጥር ወይም መታወቂያ ወይም ስምና አድራሻ የተመዘገበ ከሆነ ባለ ፈጣን መላሽ የወረቀት/ማንዋል ደረሰኝ በኤሌክትሮኒክ ደረሰኝ መመዝገቢያ ሥርዓት ሲመዘገብ የምዝገባው መረጃ በዲጂታል አማራጮች ለገዢው እንዲደርሰው ማድረግ አለበት።

3/ Pursuant to sub-article (1)(b) of this Article, if resolving the problem takes more than seven days, the taxpayer shall utilize another sales register system either on a temporary or permanent basis;

4/ Notwithstanding the provisions of sub-article (3) of this Article, the Authority may, depending on the taxpayer’s circumstances and the extent of the problem, specially adjust the duration for using manual paper invoices with Quick Response (QR) codes.

5/ A taxpayer who has utilized manual paper invoices with Quick Response (QR) codes as authorized under this Article shall:

a) Shall, within 72 hours after the problem is resolved and the connection with the Electronic Invoice Registration System is restored, register all transactions executed through manual QR-code invoices into the Authority's Electronic Invoice Registration System, referencing each manual invoice number.

b) Where the buyer's Taxpayer Identification Number (TIN), ID, or name and address are recorded, the taxpayer shall ensure that the digital record of the manual QR-code invoice is delivered to the buyer through digital means upon registration in the Electronic Invoice Registration System.

ሐ) የተመዘገበውን የኤሌክትሮኒክ ደረሰኝ ገዢው በጠየቀ ጊዜ ደረሰኙን የወረቀት ደረሰኝ ዲጂታል ቅጅ እና በድጋሚ የታተመ መሆኑን በግልጽ የሚያሳይ ምልክት በማድረግ አትሞ መስጠት ወይም በዲጂታል አማራጮች ለገዥው እንዲደርሰው ማድረግ አለበት።

c) Upon the buyer's request, the taxpayer shall provide a printed digital copy of the registered electronic invoice, clearly marked as a "DUPLICATE" copy, or deliver it to the buyer through digital means.

23. የኤሌክትሮኒክስ ደረሰኝ ሥርዓት ተጠቃሚ ታክስ ከፋይ ኃላፊነት

23. Obligations of a Taxpayer Using the Electronic Sales Register System

የኤሌክትሮኒክስ ደረሰኝ ሥርዓት ተጠቃሚ ታክስ ከፋይ የሚከተሉት ኃላፊነቶች ይኖርበታል፤

1/ የኤሌክትሮኒክ ደረሰኝ እንዲጠቀም የተፈቀደለት ታክስ ከፋይ ለሚያደርገው ማንኛውም ሽያጭ የተመዘገበ የኤሌክትሮኒክ ደረሰኝ መስጠት አለበት።

2/ የታክስ ባለስልጣኑ በማንኛውም ሰዓት በታክስ ከፋዩ የሽያጭ መመዝገቢያ ሥርዓት ላይ ፍተሻ በሚያከናውንበት ጊዜ ተገቢውን መረጃ የመስጠት፣ የባለስልጣኑ ሰራተኞች ሥርዓቱን እንዲያዩ/እንዲፈትሹ ፈቃድ የመስጠት እና ለሂደቱ ትብብር የማድረግ ግዴታ አለበት።

3/ በግብይት ወቅት ገዥው በደረሰኙ ላይ ማንነቱን የሚገልጽ መረጃ፣ የመታወቂያ ቁጥር ወይም የስልክ ቁጥር እንዲመዘገብለት ከጠየቀ መመዝገብ ግዴታ አለበት።

4/ የተፈቀደው የኤሌክትሮኒክ ደረሰኝ ሥርዓት ከታክስ ባለስልጣኑ የኤሌክትሮኒክ ደረሰኝ ምዝገባ ሥርዓት ጋር መገናኘት በማይችልበት ጊዜ የተደረጉ ግብይቶችን በሙሉ ከኤሌክትሮኒክ ደረሰኝ ምዝገባ ሥርዓት ጋር እንደተገናኘ በ72 ሰዓት ውስጥ

A taxpayer utilizing the Electronic Invoicing System shall have the following obligations:

1/ A taxpayer authorized to use the Electronic Invoicing System shall issue a registered electronic invoice for every sale made.

2/ A taxpayer shall have the obligation to provide appropriate information, grant access to the Authority's employees to view or inspect the system, and cooperate in the process whenever the Tax Authority conducts an inspection of the sales register system at any time.

3/ If, during a transaction, the buyer requests that their identity information, identification number, or telephone number be recorded on the invoice, the taxpayer shall have the obligation to record such information.

4/ Where the authorized electronic invoicing system is unable to connect with the Authority's electronic invoice registration system, the taxpayer shall ensure

መመዝገቡን እና ለገዥው ኤሌክትሮኒክ ደረሰኝ መስጠቱን ማረጋገጥ አለበት።

that all transactions conducted during such period are registered within 72 hours of the restoration of the connection, and that the electronic invoices are delivered to the buyer.

5/ የኤሌክትሮኒክ ደረሰኝ ሥርዓት እንዲጠቀም የተፈቀደለት ታክስ ከፋይ በባለስልጣኑ ያልተፈቀደ ማንኛውንም አይነት የሶፍትዌር ለውጥ እና ማሻሻያ ማድረግ አይችልም።

5/ A taxpayer authorized to use the Electronic Invoicing System is prohibited from making any type of software change or modification not authorized by the Authority.

ክፍል አምስት

ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

SECTION FIVE

Miscellaneous Provisions

24. የአቅራቢነት ፈቃድ አስገዳጅ ስለሚሆንበት

በዚህ መመሪያ አንቀጽ 8 መሰረት ለሚሰጥ አገልግሎት ታክስ ከፋዩ አገልግሎቱን የገዛው ከሀገር ውስጥ ወይም በቋሚነት ከሚሰራ ድርጅት ከሆነ አልሚው የአቅራቢነት ፈቃድ የማውጣት ግዴታ አለበት፣

24. Mandatory Requirement for Supplier Authorization

Pursuant to Article 8 of this Directive, the taxpayer that purchase from local developer or permanent establishment; the developer shall have a supplier authorization license.

25. የታክስ ዴቢት ወይም ክሬዲት ደረሰኝ

1/ ታክስ ከፋይ የሽያጭ መመዝገቢያ ሥርዓቱን አገልግሎት በመጠቀም እና በታክስ ዴቢት ወይም በታክስ ክሬዲት ደረሰኝ አማካኝነት የሽያጭ ዋጋ ማስተካከያ ማድረግ ይችላል፤

2/ ባለስልጣኑ ልዩ ልዩ መስፈርቶችን በመጠቀም በሽያጭ መመዝገቢያ ሥርዓት የሚከናወነውን የታክስ ዴቢት እና ታክስ ክሬዲት ደረሰኝ መጠን እና ጊዜ ላይ ገደብ ሊጥል ይችላል፣

25. Tax Debit or Credit Note

1/ A taxpayer may perform sales price adjustments using the sales register system through the issuance of Tax Debit or Tax Credit Notes.

2/ The Authority may, using various criteria, impose limitations on the amount and timing of Tax Debit

and Tax Credit Notes processed through the sales register system.

26. የተመዘገበን የኤሌክትሮኒክ ደረሰኝ ስለመሰረዝ

1/ ግብር ከፋዩ በተመዘገበ ኤሌክትሮኒክ ደረሰኝ ላይ የገዥ ታክስ ከፋይ መለያ ቁጥር፣ ስም እና የአድራሻ መረጃ ስህተት ወይም እቃ ወይም አገልግሎት መረጃ ስህተት ወይም የደረሰኝ ምዝገባ ድግግሞሽ ሲያጋጥም ወይም ሌላ በታክስ ክሬዲት ወይም በታክስ ዴቢት ደረሰኝ ሊስተካከል የማይችል ስህተት ሲያጋጥመው የደረሰኝ ስረዛ ጥያቄ ከነምክንያቱ በኤሌክትሮኒክ ደረሰኝ ሥርዓት ሊያቀርብ ይችላል።

2/ የኤሌክትሮኒክ ደረሰኝ ስረዛ ጥያቄ ስህተቱ እንደታወቀ ለታክስ ባለስልጣኑ በኤሌክትሮኒክ ዘዴ መቅረብ አለበት።

3/ ባለስልጣኑ የደረሰኝ ስረዛ ጥያቄ ለማጣራትና ለማረጋገጥ ተጨማሪ ማስረጃዎችን ከጠየቀ ጥያቄው በቀረበ በ48 ሰዓት ግብር ከፋዩ መልስ መስጠት አለበት፡፡

4/ የደረሰኝ ስረዛው ጥያቄ ተቀባይነት የሚኖረው በባለስልጣኑ ሲጸድቅና በኤሌክትሮኒክ ደረሰኝ መመዝገቢያ ስርዓቱ ላይ ሲመዘገብ ብቻ ነው።

5/ የገዢው የታክስ ከፋይ መለያ ቁጥር ወይም መታወቂያ ወይም ስምና አድራሻ የተመዘገበ ከሆነ የደረሰኝ ስረዛ ጥያቄ ሲቀርብ እንዲሁም ስረዛው ሲጸድቅ መረጃ በዲጂታል አማራጮች ለገዥው እንዲደርሰው ማድረግ አለበት።

26. Cancellation of a Registered Electronic Invoice

1/ A taxpayer may submit a cancellation request, along with justifications, through the Electronic Invoice Registration System in cases of errors in the buyer's TIN, name, or address; errors in the description of goods or services; duplicate invoice registrations; or other errors that cannot be corrected through a Tax Credit or Tax Debit Note.

2/ A request for electronic invoice cancellation shall be submitted to the Tax Authority through electronic means immediately upon discovery of the error.

3/ If the Authority requests additional evidence to verify and confirm a request for invoice cancellation, the taxpayer shall provide a response within 48 hours from the time the request was made.

4/ A request for invoice cancellation shall only be valid upon approval by the Authority and its subsequent registration in the Electronic Invoice Registration System.

5/ Where the buyer's TIN, identification, or name and address are recorded, the taxpayer shall ensure that notifications regarding the submission of an invoice cancellation request, as well as

its approval, are delivered to the buyer through digital means.

6/ የታክስ ባለስልጣኑ ልዩ ልዩ መስፈርቶችን በመጠቀም በሽያጭ መመዝገቢያ ሥርዓት የሚከናወነውን የደረሰኝ ስረዛ ጥያቄ ብዛት፣ የግብይት መጠን እና የስረዛ መጠየቂያ ጊዜ ላይ ገደብ ሊያደርግ ይችላል፣

6/ The Authority may, using various criteria, impose limitations on the frequency of invoice cancellation requests, the transaction volume, and the timeframe for submitting cancellation requests through the sales register system.

27. <u>የታክስ ከፋዩ ተጠያቂነት</u>

1/ በኤሌክትሮኒክ ሽያጭ መመዝገቢያ ሥርዓት የተመዘገበ የኤሌክትሮኒክ ደረሰኝ ወይም የሰጠውን ባለ ፈጣን መላሽ የማኑዋል ደረሰኝ በኤሌክትሮኒክ ደረሰኝ መመዝገቢያ ሥርዓት ካላስመዘገበ፣

2/ የደረሰኞችን መረጃ ቀይሮ ቢገኝ፤ ወይም ከባለስልጣኑ እውቅና ውጭ የሽያጭ መመዝገቢያ ሥርዓቱን መረጃ ካጠፋ፣

3/ የተመዘገበው የኤሌክትሮኒክ ደረሰኝ ወይም የማንዋል ደረሰኝ ለገዥው ከተሰጠው መረጃ ጋር ልዩነት ካለው፣

4/ ታክስ ከፋዩ ለራሱ ብቻ እንዲጠቀምበት ያስፈቀደውን የሽያጭ መመዝገቢያ ሥርዓት ከባለስልጣኑ እውቅና ውጭ ለሶስተኛ ወገን አስተላልፎ ቢሰጥና አገልግሎት ላይ ቢውል ወይም ሊውል ሲል ቢደረስበት እንዲሁም፣

5/ ከዚህ መመሪያ ጋር የሚቃረን ማንኛውንም ተግባር ፈፅሞ ቢገኝ ወይም በዚህ መመሪያ የተቀመጠውን ግዴታ ካልተወጣ፤ በታክስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 983/2008 ላይ በተደነገገው መሰረት አስተዳደራዊ ቅጣት እና እንደሁኔታው የወንጀል ኃላፊነትም ይኖርበታል።

27. <u>Liability of the Taxpayer</u>

1/ Where a taxpayer fails to register an electronic invoice issued through the electronic sales register system, or a manual invoice containing a Quick Response (QR) Code, in the electronic invoice registration system,

2/ Where it is found that invoice information has been altered, or where sales register system data has been deleted without the authorization of the Authority,

3/ Where there is a discrepancy between the data recorded in the electronic invoice or manual invoice and the information provided to the buyer,

4/ Where a taxpayer transfers the sales register system authorized for their exclusive use to a third party without the prior approval of the Authority, and such system is found to be in use or prepared for use,

5/ Any person who commits an act in violation of this Directive or fails to discharge the obligations set forth herein shall be subject to administrative penalties and, as the case may be, criminal

liability in accordance with the Tax Administration Proclamation No. 983/2016.

28. የሽያጭ መመዝገቢያ ሶፍትዌር እና አገልግሎት አቅራቢዎች ተጠያቂነት

1/ ሽያጭ መመዝገቢያ ሶፍትዌር፣ አገልግሎት አቅራቢዎች እና የኢኮሜርስ እና ዲጂታል ገበያ ቦታ አገልግሎት አቅራቢዎች በዚህ መመሪያ የተጣለባቸውን ግዴታዎች ካልተወጡ ያስያዙት ዋስትና የሚወረስ መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ አግባብነት ባላቸዉ ህጎች መሰረት የወንጀልና የፍትሐ ብሔር ተጠያቂነት ይኖርባቸዋል።

2/ በኤሌክትሮኒክ ደረሰኝ መመዝገቢያ ሥርዓት እና በግብር ከፋዩ የሽያጭ መረጃ መካከል ልዩነት ከተፈጠረ እና ለልዩነቱ መፈጠር ምክንያት የሆነው የሥርዓቱ አቅራቢ ወይም የሥርዓቱ ጉድለት መሆኑ ከተረጋገጠ አግባብነት ባላቸው ህጎች ተጠያቂ ይሆናል።

28. Liability of Sales Register Software and Service Providers

1/ Where sales register software providers, service providers, and e-commerce or digital marketplace service providers fail to discharge their obligations under this Directive, they shall be subject to criminal and civil liability in accordance with relevant laws, without prejudice to the forfeiture of the security bond deposited.

2/ Where a discrepancy is identified between the electronic invoice registration system and the taxpayer's sales records, and it is established that such discrepancy is caused by the system provider or a technical defect in the system, the provider shall be held liable in accordance with relevant laws.

29. የመሸጋገሪያ ድንጋጌ

1/ ከኤሌክትሮኒክ ደረሰኝ መመዝገቢያ ሥርዓት ተስማሚ የሆነ የሽያጭ መመዝገቢያ ስርዓት መጠቀም በሁሉም የሂሳብ መዝገብ በሚይዙ ታክስ ከፋዮች አስገዳጅ ሲሆን ትግበራው ባለስልጣኑ በሚያወጣው መርሐ ግብር መሰረት የሚተገበር ይሆናል።

2/ የታክስ ደረሰኝ አጠቃቀም እና አስተዳደር መመሪያ ቁጥር 149/2011 ወይም በፍትህ ሚኒስቴር የመመሪያው ምዝገባ ቁጥር 165/2011 መሰረት የሽያጭ መመዝገቢያ

29. Transitional Provisions

1/ The use of a compliant sales register system within the electronic invoice registration framework is mandatory for all taxpayers who are obligated to maintain books of accounts. Implementation shall be carried out in accordance with the schedule issued by the Authority.

2/ Taxpayers who are obligated to use sales register software pursuant to the Tax Invoice Utilization and Administration

ሶፍትዌር እንዲጠቀሙ ግዴታ ያለባቸው ታክስ ከፋዮች በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 በሚኖረው መርሐ ግብር መሰረት የኤሌክትሮኒክ ደረሰኝ መመዝገቢያ ሥርዓት የሚጠይቀውን መስፈርት የሚያሟላ የሽያጭ መመዝገቢያ ሶፍትዌር/ስርዓት መጠቀም አለባቸው።

Directive No. 149/2018 (Ministry of Justice Registration No. 165/2018) shall adopt a sales register software/system that fulfills the requirements of the electronic invoice registration system, in accordance with the schedule stipulated under sub-article 1 of this Article.

30. የተሻሩ መመሪያዎችና ተፈጻሚነት የሌላቸው አሠራሮች

1/ የታክስ ደረሰኝ አጠቃቀም እና አስተዳደር መመሪያ ቁጥር 149/2011 ወይም በፍትህ ሚኒስቴር የመመሪያው ምዝገባ ቁጥር 165/2011 ስለ ኤሌክትሮኒክ ደረሰኝ የተደነገጉት አንቀጽ 8 እና አንቀጽ 23 በዚህ መመሪያ ተሽረዋል።

2/ ይህን መመሪያ የሚቃረን ማንኛውም መመሪያ ወይም አሰራር ተፈጻሚነት የለውም።

31. መመሪያው የሚፀናበት ጊዜ

ይህ መመሪያ በፍትህ ሚኒስቴር ከተመዘገበበት እና በገቢዎች ሚኒስቴር ድህረ-ገጽ ላይ ከተጫነበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል።

30. Repealed Directives and Inapplicable Practices

1/ Article 8 and Article 23 of the Tax Invoice Utilization and Administration Directive No. 149/2018 (Ministry of Justice Registration No. 165/2018), which pertain to electronic invoices, are hereby repealed by this Directive.

2/ Any directive or practice inconsistent with this Directive shall not be applicable.

31. Effective Date

This Directive shall enter into force as of the date of its registration by the Ministry of Justice and its publication on the website of the Ministry of Revenues.

አዲስ አበባ፤ ሐምሌ፣ 2018 ዓ.ም.

አይናለም ንጉሴ አሊ

የገቢዎች ሚኒስቴር ሚኒስትር

Addis Ababa, June, 2026 G.C.

Aynalem Nigussie Ali
Minister, Ministry of Revenues

አባሪ 1

የደረሰኝ ናሙና አባሪ 1

……

……………………………………………………………………………………………………..

አባሪ 2፡ የሽያጭ መመዝገቢያ ሥርዓት ከቀጥታ ግንኙነት ውጭ ሥራ ማስቀጠያ (offline) አገልግሎት እንዲኖረው አስገዳጅ የሚሆንባቸው የሥራ ዘርፎች

ተቁ	የንግድ ዘርፍ	
1.	Retail sale of food	የምግብ ችርቻሮ ንግድ
2.	Retail sale of beverages	የመጠጥ ችርቻሮ ንግድ
3.	Retail sale of tobacco products	ሲጋራና የሲጋራ ውጤቶች ችርቻሮ ንግድ
4.	Retail sale of automotive fuel	የነዳጅና ነዳጅ ውጤቶች ችርቻሮ ንግድ
5.	Retail sale of textiles	የጨርቃጨርቅ ችርቻሮ ንግድ
6.	Retail sale of books, newspapers, stationery and office supplies	የመጸሃፍት፣ ጋዜጦች፣ የጽህፈት መሳሪያዎችና የቢሮ እቃዎች ችርቻሮ ንግድ
7.	Retail sale of clothing, footwear and leather articles	ልብስ፣ ጨርቃጨርቅና የቆዳ ውጤቶች ችርቻሮ ንግድ
8.	Retail sale of pharmaceutical and medical goods, cosmetic and toilet articles	መድሃኒቶች፣ የህክምና መሳሪያዎች፣ የውበትና ንፅህና መጠበቂያ ምርቶች ችርቻሮ ንግድ
9.	Retail sale of other new goods	ሌሎች የአዲስ እቃዎች ችርቻሮ ንግድ
10.	Retail sale of second-hand goods	ሌሎች ያገለግሉ እቃዎች ችርቻሮ ንግድ
11.	Retail sale of motor vehicles, motorcycles and related parts and accessories	የተሽከርካሪዎችና ባለሞተር ብስክሌቶች መለዋወጫ የችርቻሮ ንግድ
12.	Passenger rail transport, interurban	የከተማ ለከተማ ባቡር ትራንስፖርት
13.	Urban and suburban passenger land transport	የከተማና የንዑስ ከተማ የመንገደኞች ማጓጓዣ
14.	Other passenger land transport	ሌሎች የመንገደኞች ማጓጓዣ
15.	Postal activities	የመልዕክት አገልግሎት
16.	Short term accommodation activities	የአጭር ጊዜ ማረፊያ ቦታዎች ሥራዎች
17.	Camping grounds, recreational vehicle parks and trailer parks	ውጭ መዝናኛና ሽርሽር ተሽካርካሪዎችና መኪና ማቆሚያ ሌሎች አገልግሎቶች
18.	Restaurants and mobile food service activities	ምግብ ቤቶችና ተንቀሳቃሽ የምግብ አገልግሎቶች

19.	Beverage serving activities	የመጠጥ አገልግሎቶች
20.	Hospital activities	የህክምና ተቋም አገልግሎቶች
21.	Medical and dental practice activities	የህክምና እና የጥርስ አገልግሎት
22.	Hairdressing and barber activities	የጸጉር ውበትና ጸጉር ማስተካከል ስራዎች
23.	Beauty care and other beauty treatment activities	የውበት መጠበቂያና ሌሎች የውበት እንክብካቤ ስራዎች
24.	Day spa, sauna and steam bath activities	የፍል ውሃ፣ ሳውና እና እጥበት አገልግሎቶች
25.	Veterinary activities	የእንሣት ህክምና
26.	Activities of amusement parks and theme parks	የመዝናኛ ቦታዎች